# የጋብቻ ዝግጅት

እሳት ወይ አበባ

# ማውጫ


ክፍል 1 የክርስቲያን ጋብቻ ማለት ምን ማለት ነው ?

ትምህርት 1 ጋብቻ በእግዚአብሔር ሥርአት የተደነገገ ነው ። ገጽ 1

ትምህርት 2 እግዚአብሔር ስለ ጋብቻ ያለው እቅድ 2

ትምህርት 3 ሁሉም ሰው ማግባት አለባትን? 9

ክፍል 2 ለጋብቻ መዘጋጀት

ትምህርት 4 ማንን ላግባ? 15

ትምህርት 5 መቼ ማግባት ይሻለኛል? 19

ትምህርት 6 የእጮኛነት ጊዜ 24

ክፍል 3 በልምምዱ የሚገለጥ የጋብቻ ግብ

ትምህርት 7 ፍቅር ፣ መግባባትና መተማመን 29

ትምህርት 8 ክርስቶስን የሚያከብር ቤት ዋስትና 33

ትምህርት 9 መንፈሳዊ እድገት ፣ አባሪነትና ሽርክነት 37

ክፍል 4 በጋብቻ ያለ የልብ መቀራረብ ሚሥጢረኛነት

ትምህርት 10 ሚሥጢራዊ ሕብረት 42

ትምህርት 11 በጋብቻ የሚገኝ ደስታ 46

ትምህርት 12 ሠርግ 49

ክፍል 5 እንደገና መጋባት

ትምህርት 13 እንደገና መጋባት 55



ጋብቻ በእግዚአብሔር ሥርዓት የተደነገገ ነው ።

**ክፍል ፩**
**ትምህርት ፩ — ፫**
**የክርስቲያን ጋብቻ ማለት ምን ማለት ነው ?**

<u>የክፍሉ ዓላማ</u> ፡— የክርስቲያን ጋብቻ ምን እንደሆነ ለማሳየት ፥ እንዲሁም እያንዳንዳቸው ጋብቻቸውን እግዚአብሔር ወደሚወደው ዓይነት ጋብቻ እንዲመራ እንዲናፍቁ ፥ ከዚህም በቀር ስለ ጋብቻ ትክክለኛ የሆነ አስተሳሰብ እንዲኖራቸው ነው ።

<u>የክፍሉ ጥቅስ</u> ፡— ምሳሌ ፲፰ ፥ ፳፪

ክፍል ፩ — ትምህርት ፩

# ጋብቻ በእግዚአብሔር ሥርዓት የተደነገገ ነገር ነው ።

<u>የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል</u> ፡— ዘፍጥረት ፪ ፥ ፲፰ — ፳፭

<u>የቃል ጥናት</u> ፡— ዘፍጥረት ፪ ፥ ፳፬

<u>ዓላማ</u> —. ጋብቻ በእግዚአብሔር የተደነገገ ነገር ነው ።
. ያላገቡ ሰዎችም ስለ ጋብቻቸው የእግዚአብሔርን ፈቃድ መናፈቅ ፥
.ቤተሰቦች በጋብቻቸው ስለሚሰጥዋቸው ልጆች የእግዚአብሔርን ፈቃድ መናፈቅ

<u>መግቢያ</u> ፡— ጽጌ ወደ ቤትዋ በመመለስዋ ተደሰተች ። በዳር አገር ከሌሎች ተማሪዎች ጋር ከአንድ ስፍራ ወደ ሌላው በአገልግሎት ስትዘዋወር ቆየች ። አሁን ግን እንደገና ወደ ቤትዋ ተመልሳ ከእናትዋና ከአባትዋ እንዲሁም ከወንድምዋና ከሁለት እህቶችዋ ጋር መሆንዋ መልካም ነው ። ነገር ግን ጽጌ ወደ ቤትዋ በመመለስዋ ደስ ከመሰኘት ይልቅ በውስጥዋ ትታወክ ጀመር ። ምክንያቱም ወደ ሆስፒታል ተመልሳ ጀምራው የነበረውን የነርስነት ትምህርት መቀጠል ይኖርባት እንደ ሆን ስለማታውቅ ነው ። ምክንያቱም አንድ አስፈላጊ የሆነ ውሳኔ ማድረግ ስላለባት ነው ።

ጽጌ አንድ ዓመት ብቻ ከተማረች በኋላ ነው ለእናት አገር ጥሪ አገልግሎት የተሰማራችው ። እርስዋም በትምህርትዋ አስደሳች ውጤት ከማግኘትዋ በላይ ሥራዋን ትወድ ነበር ። ነገር ግን የጸሎት ሰው እንደመሆንዋ መጠን ገና ስለሚቀራት የሦስት ዓመት ጥናት ስትጸልይ ጉዳዩ ሰላም አልሰጣትም ። ወላጆችዋ አቶ ኃይሌና ወይዘሮ ጥሩነሽ የበኲር ልጃቸው ወደፊት ነርስ ስለምትሆንላቸው የልብ ኩራት ይሰማቸዋል ። እርስዋም እነርሱን እንዲከፉባት አትወድም ።

ጽጌ ወደ ትምህርት ቤት እንደምትመለስ እርግጠኛ ያልሆነችበት አንድ ምክንያት ከመመለስዋ በፊት ብዙ ወራቶች አቋርጣ ጊዜዋን በማጥፋት መጠበቅ ስለሚኖርባት ነው ። ነገር ግን በጣም አስፈላጊ ስለ ሆነ ጉዳይና በዚህም ነገር አሳብ ያለውን ሰው ጌታ መንገዱን እንዲያቃናላት ትጸልይበት የነበረችበት ጉዳይ አላት ። በዚህ እርስዋ ባሰበችው ጉዳይ ላይም ሁሉ ሰው ቅር ሳይለው ይስማማበት ዘንድ አጥብቃ ትጸልያለች ። ወጣት ጥላሁን ለረጅም ወራት ከአቶ ኃይሌ ቤተሰቦችና በተለይም ከጽጌ ጋር በወዳጅነት የቆየ ሰው ነው ። በእርግጥም ጥላሁን ልጃቸውን ጽጌን እንዲያገባ ፈቃድ ጠይቆአቸው ነበር ።

<u>ትምህርት</u> ፥— ጋብቻ «ተጠብቆ የሚኖር ነገር» እንጂ ፥ እንደ ኳስ ጨዋታ አንዱ ድል አድርጎ አንዱ ድል ተደርጎ የሚያበቃ ነገር አይደለም ። እርሱም «ለቋሚ ነገር» እንጂ ለዋዛ ስላልሆነ ሁለቱም አባሎች ጋብቻቸው ጥሩ ውጤት እንዲኖረው የተቻላቸውን ሁሉ በትጋት ሊሠሩ ይገባል ። ጋብቻ በእግዚአብሔር ሥርዓት የተደነገገና ቋሚ ነገር የሆነ ጉዳይ ነው ። ይኼም እግዚአብሔር ያቀደው ስለሆነ ወደፊት ሊናፍቁት የሚገባ ነገር ነው ። ጋብቻም ሊኖረን ይገባል ተብሎ ወደፊት በተለፉ ሊጠባበቁት የሚገባ ነገር ነው ። ምክንያቱም ለእግዚአብሔር የሰጠነው ጉዳይ በመሆኑ ነው ። ስለዚህም ጉዳይ በመጀመሪያው መጽሐፍ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንመለከታለን ። ሰው ብቻውን ይሆን



ዘንድ መልካም አለመሆኑን አውቆ እግዚአብሔር ለአዳም እረዳት ትሆነው ዘንድ ሔዋንን ፈጠረለት ። (ዘፍጥረት ፪ ፥ ፲፰) እርሱም አንድ ሥጋ አደረጋቸው ። (ዘፍጥረት ፪ ፥ ፳፫ — ፳፬ እንብብ ።) ሴትና ወንድ አንድነት ሲሆኑ ፍጹም ሕብረትን ይፈጥራሉ ። እነርሱም አብረው በመሥራት አብረው በመጸለይና ክፉውንና ደጉን በአንድነት በመቀበል ትክክለኛ ሕብረትን በመፍጠር ተጣምረው ይኖራሉ ። እንደ እግዚአብሔር ውጥን የሚደረጉ ጋብቻዎች ፍጹም አንድነት ይፈጥራሉ ። (ማቴዎስ ፲፱ ፥ ፭ ፤ ኤፌሶን ፭ ፥ ፴፩ ።) እግዚአብሔርም ችሎታቸውን ልባቸውንና እቃማቸውን ወስዶ አንድ ላይ ያጣምራቸዋል ። ይኼም ደግሞ ሥጋዊና መንፈሳዊ አንድነት ይሰጣቸዋል ። ይህም የተለየ ቅዱስ ነገር ነው ።

እግዚአብሔር ሔዋንን ለአዳም እረዳትነት እንደፈጠራት ሁሉ (፩ኛ ቆሮንቶስ ፲፩ ፥ ፱) ሌሎችም ሴቶች በሞላ ለባሎቻቸው እረዳት መሆን አለባቸው ። እነርሱም በአንድነት እንዲሠሩ አደረጋቸው ። እግዚአብሔርም ሴትን ከአዳም ከክንዱ በታችና ከልቡ አጠገብ ከሚገኘው አጥንት ሠራት ። ይኸውም እንዲወዳት ሲሆን ከክንዱ በታች መሆኑ ደግሞ እንዲያቅፋት ነው ። እርሱም በመንፈስም ሆነ በሥጋ እንዲቀራረቡ ይፈልግባቸዋል ።

ጋብቻ ይሉአችኋል ይህ ነው ! ጋብቻ በቀላሉ የሁለት ተዋዳጅ ሰዎች ሕብረት ማለት ነው ። እንደዚህ ያሉት ሰዎች ሞት እስከሚለያቸው ድረስ ሕይወታቸውን በአንድነት አጣምረው ይኖራሉ ። እግዚአብሔርም አንድነቱን በሕይወት ዘመን ሁሉ እንዲቆይ ይፈልጋል ። (ማርቆስ ፲ ፥ ፱ — ፲፪) እግዚአብሔር ያጣመረውን የጋብቻ ሕብረትን የሚያቋርጠው ሞት ብቻ ነው ። ጋብቻም ቋሚ የሆነ ሕብረት ነው ። ይኸውም አንድ ሴትና አንድ ወንድ ብቻ አብረው የሚሆኑበት ነው ። ነገር ግን አንድ ወንድና ብዙ ሴቶች አብረው የሚሆኑበት ወይም አንድ ሴትና ብዙ ወንዶች አብረው የሚሆኑበት አይደለም ። እግዚአብሔር ለአዳም አንድ ሴት ብቻ ነው የፈጠረለት ።

አንድ ሰው ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት በሚሾምበት ጊዜ የአንዲት ሚስት ባል እንዲሆን ቅዱስ ጳውሎስ ያዛል ። (፩ኛ ጢሞቴዎስ ፫ ፡ ፲፪) የመጽሐፍ ቅዱስ ምሳሌዎችንና የአንዳንድ ሰዎችን ታሪክ ስናነብ በዚህ ነገር ያልታዘዙ ሰዎች ሁሉ ብዙ ኀዘንና ችግር እንደደረሰባቸው ተምረናል ። ይህንንም በአብርሃም ታሪክ ውስጥ እንመለከታለን ። በአጋርና በሳራ መካከል ብዙ ጥልና ክርክር ነበረ ። (ዘፍጥረት ፲፮ ፤ ፩ኛ ቆሮንቶስ ፯ ፡ ፪)

የክርስቲያን ጋብቻ ማለት ባልና ሚስት ተገቢ በሆነ መንገድ የሚጣመሩበትና ሕብረታቸውን በአግባብና በፍቅር የሚያስተባብሩበት ዓይነተኛ መንገድ ነው ።

<u>ትምህርቱን በሥራ ላይ ማዋል</u> ፦

ጽጌ ቀደም ብላ የነርስነት ትምህርት ስለጀመረች ትምህርትዋን መጨረስ ይኖርባታል ወይንስ ማግባት አለባት ? (ውይይት ።) ጽጌ ስለ ወደፊት ኑሮዋ መጸለይዋን የቀጠለች ቢሆንም ቤተሰቦችዋም ሆኑ ጥላሁን በጸሎታቸው ጉዳዩን ለእግዚአብሔር ማቅረባቸውን አላቋረጡም ። ጽጌ ቤተሰቦችዋን ሳታማክር አንዳች ነገር ማድረግ አትፈልግም ። አቶ ኃይሌና ወይዘሮ ጥሩነሽ ልጃቸው ነርስ ብትሆንላቸው ይወዳሉ ፤ ከዚህ የላቀ ግን እግዚአብሔር ለሕይወትዋ ያቀደላት ነገር ቢፈጸም ይበልጥ ደስ ይላቸዋል ። እነርሱም እግዚአብሔር ማንኛውንም ሰው በትምህርቱ እንዲቀጥል እንደሚመራው ተገንዘቡ ። እግዚአብሔር ለእያንዳንዱዋ ልጅአገረድ ያለው እቅድ አንድ እንዳይደለም ያውቃሉ ። እነርሱም ከልጃቸው ጋር ሆነው እግዚአብሔር ስለ ጋብቻ ምን እንደሚል ለማወቅ መጽሐፍ ቅዱሳቸውን ማጥናት ጀመሩ ። ከዚያም ምክርና እርዳታን ከእግዚአብሔር ቃል እንዲሰጥዋቸው የቤተ ክርስቲያናቸው መጋቢ ወደ ሆኑት ወደ አቶ ደስታ ዘንድ ሄዱ ። ጌታ ልጃቸው እንድታገባ የሚፈቅደው አሁን ከሆነ እርሱን የሚያስከብር ጋብቻ እንድ ትመሠርት ሊረዱዋት ቁርጥ ውሳኔ አደረጉ ።



<u>ጸሎት</u> ፦ እግዚአብሔር ስለሰጣቸው የኑሮ ጉዋደኛ እያንዳንዳቸው ባልና ሚስቶች እግዚአብሔርን ያመስግኑ ።

ሴቶች ለባሎቻችሁ ረዳት ናችሁን ? እግዚአብሔር አንድ እንዲያደርጋችሁ ጠይቁት ።

ወላጆችም ለልጆቻቸው ወደፊት ለጋብቻቸው ቀን እርሱ የኑሮ ጓደኛ እንዲያዘጋጅላቸው እያንዳንዳቸውን በስም እየጠሩ ይጸልዩላቸው ። ሕፃናትም እንኳ ቢሆኑ ወደፊት ሊያደርጉት ስላለ ስለዚህ አስፈላጊ ነገር ሊጸለይላቸው ይገባል ።

### ክፍል ፩ — ትምህርት ፪

## እግዚአብሔር ስለ ጋብቻ ያለው እቅድ

<u>የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል</u> ፦ ዘፍጥረት ፳፬ ፡ ፴፪ — ፷

<u>የቃል ጥናት</u> ፦ መዝሙር ፻፳፯ (፻፳፮) ፡ ፫

<u>ዓላማ</u> —.እግዚአብሔር ስለ ጋብቻ ያለውን አመራር ለማሳየት ፤
.እያንዳንዱ ሰውም በጋብቻው ጊዜ በዚህ መመሪያ እንዲጠቀም ለማድረግ

<u>መግቢያ</u> ፦ ጥላሁን በመንግሥት ሥራ ምክንያት ወደ ከተማ ከተቀየረ ወዲህ ለሁለት ዓመት ጊዜ ወደ ሚያውቃቸው ወደ መጋቢ ደስታ ዘንድ ሄደ ። እርሱም ከመጋቢውና ከቤተሰባቸው ጋር ስላለው ሕብረትና ስለ ቤተ ክርስቲያኒቱ በጣም ደስ ብሎታል ። መጋቢ ደስታ የጽጌ ቤተሰቦች ደግሞ በጉዳዩ ከእርሳቸው ጋር መወያየታቸውን ለጥላሁን ነገሩት ። ከዚያም መጋቢ ደስታ ጥላሁንና ጽጌ ወደ እርሳቸው ዘንድ መጥተው ስለዚሁ ጉዳይ እንዲወያዩም ሀሳብ አቀረቡ ። ጽጌና ጥላሁንም በዚህ በጋብቻቸው ጉዳይ ጌታ መንገዱን እየከፈተላቸው እንደ ሆነ አመኑ ። እርሱም አቶ ኃይሌ በጋብቻቸው እንዲስማሙ አስቦ ነበር ። በእርግጥ ተስፋ ያደርጋል ። ጥላሁ

ንም እግዚአብሔር ስለ ጋብቻ ያለውን አመራር ለማወቅ በጣም ፍላጎት ነበረው ። ቀድሞ ግን ስለዚህ ጉዳይ ብዙ ሀሳብ አልነበረውም ።

ትምህርት ፡— በጋብቻ በሚጣመሩ ሰዎች መከከል እግዚአብሔር የሚፈጽመው ጥቂት ግሩም የሆነ እቅድ አለው ። ይሄም ደግሞ ወደ መልካም የጋብቻ ፍጻሜ ለመድረስ እግዚአብሔር ያዘጋጀው አንድ ብቻ የሆነ መንገድ ነው ።

እግዚአብሔር የጋብቻን እቅድ ያወጣበት አንደኛው ምክንያት የክርስቲያኖችን ቤት ለመመስረት ነው ። በዘፍጥረት ፳፬ ላይ የርብቃ አባት የአብርሃምን ልጅ ይስሐቅን እንድታገባ ከአብርሃም ሎሌ ጋር እቅድ እንዳወጡ እናነባለን ። አገራቸው በጣም የተራራቀ ነው ። ስለዚህ ርብቃ ይስሐቅን ካገባች ቤተሰቦችዋን ዳግመኛ አታያቸውም ። እነርሱም ፡— «ከዚህ ሰው ጋር ትሄጃለሽ ?» ብለው ጠየቅዋት ። እርስዋም ያለ አንዳች ቅሬታ ፡— «እሄዳለሁ» ብላ መለሰችላቸው ። ልጅቱ ከዚያ ከሰው ጋር በመኖር ቤተሰብን ለመመስረት ፈቃደኛ እንደሆነች መጠየቅ ተገቢ ነበር ። የቀረውን የሕይወትዋን ዘመን የሚነካ ውሳኔ ነበር የምትወስነው ። ስለዚህ ከራስዋ ፈቃድ ውጭ የሆነ ውሳኔ እንድትወስን መገደድ አልነበረባትም ።

ጋብቻ የቤተሰብ መሠረት ነው ። የክርስቲያንም ቤት ሰላም ፣ ፍቅር ፣ ትእግስትና መግባባት ሊታይበት የሚገባው ነው ። ባለፈው በትምህርታችን መጨረሻ ላይ የጠቀስነው ጥቅስ አንድ ስለ ጋብቻ የሚጠቅስልን አስፈላጊ ሀሳብ አለ ። ያ ነገር ምንድር ነው እሱ ? አንድ ሰው ሚስት በሚያገባበት ጊዜ ቤተሰቦቹን መተው አለበት ። (ዘፍጥረት ፪ ፡ ፳፬) ሴቲቱም ስታገባ ልክ እንደ ርብቃ ቤተሰቦችዋን መተው አለባት ። ይኸንንም ስንል ጨርሳ ትርሳቸው ወይም አንድነት አይኑራት ማለታችን አይደለም ። ነገር ግን በቀድሚያ ባልዋን በማክበር ትደግፈዋለች ። እግዚአብሔር ባልና ሚስቶች እንዲዋደዱ ፣



እንዲረዳዱና እርስ በእርሳቸው እንዲደጋገፉ ይፈልግባቸዋል ። ሚስጢራዊ ስለሆኑ ነገሮች በስውር ሊወያዩና ሊመከከሩ አብረውም እቅድ ሊያወጡ ይገባል ። ሌሎች ሰዎች በቤታቸው የሚኖሩ ከሆነ ይህንን ዓይነት ሚስጢራዊ ነገር ሊወያዩ አይችሉም ።

ሌላው እግዚአብሔር ለጋብቻ ያቀደው ነገር ደግሞ ልጆች እንዲወለዱ ነው ። ይኸውም የክርስቲያን ቤተሰብ እንዲመሰረት ነው ። (ዘፍጥረት ፩ ፡ ፳፯ — ፳፰) ልጆች ከእግዚአብሔር የተሰጡ ስጦታዎች ስለሆኑ ሴቲቱም ሆነ ወንድየው ልጆች በመውለዳቸው እድለኛነት እንደሆነ ቢገምቱትም ለጌታ ክብር የሚኖሩ ልጆች አድርጎ የማሳደግ ኃላፊነትም እንዳለባቸውም ማወቅ ይኖርባቸዋል ። ልጆች ያልተወለዱባቸውም ብዙ ቤቶች አሉ ። ይህ ስለሆነ ሰውዬው ሚስቱን ትቶ ሌላ ይፈልግ ማለት አይደለም ፣ ወይም ደግሞ ሴቲትዋ ባልዋን ትታ ሌላ ትፈልግ ማለት አይደለም ። እግዚአብሔር ፣ ያለቤተ ሰብ ለእርሱ ምስክሮች እንዲሆኑ አቅዶ ሊሆን ይችላል ። ምናልባትም ልጆች ስለአልወለዱ ለእግዚአብሔር በተለየ መንገድ እንዲያገለግሉት አስቦ ይሆናል ። ዋንኛው ቁም ነገር ግን እርሱ ያለውን መቀበል ነው ። እርሱ ፍላጎታቸውን ስለሚያውቅ አስቦ ያቀደላቸው ነገር ሁሉ ፍጹም ነው ። እርሱ ችሎታቸውን ደግሞ ስለሚያውቅ የሚጠቅማቸውን መርጦ ይሰጣቸዋል ።

እግዚአብሔር ጋብቻን ያቀደበት ሌላው ምክንያት ደግሞ ክርስቲያን ቤተሰቦች ጠንካራ ቤተ ክርስቲያንን እንዲመሰርቱ ነው ። በ፩ኛ ጢሞቴዎስ ምዕራፍ ፫ ላይ የቤተ ክርስቲያን መሪ ምን ዓይነት ችሎታዎች ሊኖሩት እንደሚገባ ተጠቅሶአል ። (ቁጥር ፪ ና ፬ ና ፭ አንብብ ።) ቤተሰባቸውን እንዴት አድርገው ማስተማርና መምራት እንዳለባቸው መመሪያ ተሰጥቶአቸዋል ። ጋብቻ የቤተሰብ መሠረት እንደመሆኑ መጠን ቤተሰብ ደግሞ የቤተ

ክርስቲያን መሠረት ነው ። ምክንያቱም የቤተ ክርስቲያን ሥራ የሚካሄደው በእያንዳንዱ ቤተሰብ ሕብረት ስለሆነ ነው ። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አገልግሎት የሚሰጡ ብዙ ያላገቡና የበሰሉ ሰዎች አሉ ። ያላገባ ሰው ቤተሰብ እንዳላቸው ሰዎች ሕብረተሰቡን አይመሠርትም ። ጠንካራ ቤተ ክርስቲያን ቋሚ ባልሆነ ተዘዋዋሪ ቤተሰቦች ልትመሰረት አትችልም ። በአንድ ቦታ መጽናትና ሥራውን ወደፊት መቀጠል ያስፈልጋል ። አንዳንድ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚገቡ ጉዳዮች ስላሉ በአገቡ ሰዎች ጉዳዩ ቢጠናና ሥራው ቢካሄድ መልካም ነው ። ያላገባ ሰውም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለሚሠሩ ነገሮች ሰፊ ድርሻ አለው ። ነገር ግን ትክክለኛዎቹ የቤተ ክርስቲያን መሠረቶች ክርስቲያን ቤተሰቦች ናቸው ።

<u>ትምህርቱን በሥራ ላይ ማዋል</u> ፦

ጥላሁንና ጽጌ ከመጋቢ ደስታ ጋር ለመነጋገር ሄዱ ። በፊት እግዚአብሔር ስለ ጋብቻ የተናገራቸውን ጉዳዮች ነገሬ ብለው አልተከታተሉም ነበር ። በኋላ ግን እንዴት ያለ ታላቅ ኃላፊነትን የሚጠይቅና በሕይወታቸው አድርገውት የማያውቁት አስፈላጊና ቁም ነገር የሆነ ጉዳይ እንደሆነ ተገነዘቡ ። ከዚያም ከመጋቢ ደስታ ጋር ሆነው እነርሱ ለጋብቻቸው ያቀዱት እቅድ ጌታ እንዳቀደላቸው እንዲሆን እንዲረዳቸው ጸለዩ ።

ከመጋቢ ደስታ ዘንድ ከወጡ በኋላ ወደነ ጽጌ ቤት ሄደው ሲነጋገሩበት ስለቆዩት ጉዳይ ከቤተሰቦችዋ ጋር መወያየት ጀመሩ ። በውይይታቸውም ውስጥ ስለ መጋባታቸውም ጠቅሰው ነበር ። በዚሁ በጋብቻ ጉዳይ እየተወያዩ ሳለ የጽጌ አባትና እናት አቶ ኃይሌና ወይዘሮ ጥሩነሽ ጌታ ልጃቸውንና እጮኛዋን ለጋብቻ እየመራቸው እንዳለ ተሰማቸው ። በዚያም ምሽት አቶ ኃይሌና ወይዘሮ ጥሩነሽ በእነርሱም ጋብቻ የእግዚአብሔር ፈቃድ ይበልጥ እየቀጠለ እንዲሄድ ጸለዩ ። በቤተሰባቸውና በቤተ ክርስቲያናቸው ውስጥ ያለባቸውን ኃላፊነት እንዳያፈርሱ እንዲረዳቸው አጥብቀው በጸሎት ገልጸውታል ።



እናንተስ በጋብቻችሁ የእግዚአብሔርን ፈቃድ እያሟላችሁ ነው ? የእናንተስ ቤት የክርስቲያን ቤተሰብ ነው ? ልጆቻችሁንስ በክርስቲያን እውነተኛ መመሪያ ትመሯቸዋላችሁ ? ቤተሰባችሁስ ለቤተ ክርስቲያናችሁ መጠናከር ኃይል ናቸው ? እናንተስ ድርሻችሁን አገልግሎት ትሰጣላችሁ ? ወይስ በብላሽ ዝም ብላችሁ ትቀበላላችሁ ?

<u>ጸሎት</u> ፦ እነዚህን ጥያቄዎች በማጤን ሊደረጉ የሚገባቸውን ነገሮች ከአሁኑ ጀምራችሁ እንድታደርጉ የእግዚአብሔርን እርዳታ ጠይቁ ። ለጥያቄዎቹም ከታዘዛችሁ በኋላ በጋብቻችሁ ጉዳይ ላይ ፈቃዱን እንዲያሟላ ማድረግ የሚገባችሁን እንድታደርጉ እርዳታው እንዳይለያችሁ ደግማችሁ አሳስቡ ።

ያላገባችሁ ከሆነም እግዚአብሔር ለጋብቻ ያዘጋጃችሁ ዘንድና የእርሱን ፈቃድ የምታሟሉበትን ቤት እንዲመሰርትላችሁ ጠይቁት ።

ክፍል ፩ — ትምህርት ፫

# ሁሉም ሰው ማግባት አለበትን ?

<u>የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል</u> ፦ ፩ኛ ቆሮንቶስ ፯ ፡ ፩ — ፱

<u>የቃል ጥናት</u> ፦ ማቴዎስ ፲፱ ፡ ፲፪

<u>ዓላማ</u> — . ሁሉ ሰዎች እንዲያገቡ የእግዚአብሔር ፈቃድ አለመሆኑን ለማስተማር ፣
. ላላገቡትም ሰዎች የፍቅርና የትህትናን መንፈስ እንዲያሳዩ ለመምራት

<u>መግቢያ</u> ፦ ማሚቴ የጽጌ የቅርብ ጓደኛ ናት ። እርስዋም መጋቢ ደስታ ስለ ጋብቻ መመሪያ የሰጡትን ትምህርት ተካፍላ ነበር ። አንድ ምሽት የእያንዳንዱን የተጋቢ ኃላፊነት በሚመለከት ጉዳይ ላይ ሲወያዩ ማሚቴ ጉዳዩ አስጨነቃት ። ሆኖም ነገሩ ለእርስዋም የሚያስፈልጋት እንደሆነ ብትገምትም ወዲያውኑ ልታደርገው አልፈቀደችም ። ምናልባት ከጥቂት ዓመታት

በኋላ የተለየ ሀሳብ ይሰማት ይሆናል ። ነገር ግን ለጊዜው የበለጠ ያስፈለጋት ነገር ነበር ። እርስዋና ጽጌ ለእናት ሀገር ጥሪ አገልግሎት ከመሄዳቸው በፊት በንግድ ሥራ ትምህርት ቤት ትማር ነበር ። አሁን ግን ትምህርትዋን ጨርሳ ሥራ ለመያዝ አቅዳለች ።

ለዚህ ነው እንግዲህ ፦ «ሰው ሁሉ ለማግባት ይገደዳልን ?» ብላ ለመጠየቅ የደፈረችው ። «እስከ አሁን ድረስ እኛ ስለ ጋብቻ ያለንን አስተሳሰብ ብቻ ተነጋግረናል ። ስላላገባ ሰው ምንም የተናገርነው ነገር የለም ?» በዚህን ጊዜም በብዙዎቹ ፊት ላይ የመገረም ፈገግታ ይታይ ነበር ። ምክንያቱም ገብሬ ማሚቴን ለማግባት ፍላጎት እንደነበረው ሁሉም ስለሚያውቁ ነው ። ቢሆንም ለዚያ ፍላጎቱ መልስ አልሰጠችውም ነበር ።

<u>ትምህርት</u> ፦ መጋቢ ደስታ መጽሐፍ ቅዱሳቸውን በመግለጥ ፩ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ ሰባትን እየጠቀሙ እንዲህ አሉ ፦ «በመጀመሪያ ደረጃ እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ ሰው ሕይወት እቅድ እንዳለው ማስተዋል ይኖርብናል ። ከዚህም በቀር እግዚአብሔር እኛ ያስፈልገናል ብለን ከምንወጥነው ነገር በላይ እርሱ ለእኛ የሚበጀንና መልካሙን ያውቃል ። ሕይወታችንን እርሱ በሚፈቅደው አመራር እንዲመራው መስጠት የጋራ አስተሳሰብ የሆነ ነገር ነው ። ለእያንዳንዶቹ የእርሱ አመራር ምናልባት እንዳያገቡ ይሆናል ። ለአብዛኛዎቹ ግን የእግዚአብሔር አመራር እንዲያገቡ ነው ።» ከዚያም በዚያው ምዕራፍ ከሌላ ጥቅስ ስላላገባ ሰው ምን እንደሚናገር ጠቅሰው ነገሩአቸው ።

እግዚአብሔር የወንጌልን ጥሪ በሚገባ እንዲያከናውኑ አንዳንዶቹን በብቸኝነት ይጠራቸዋል ። በአንዳንድ ሰዎች ዘንድ ጳውሎስ እንዳላገባ ይታመናል ። ምክንያቱም በቁጥር ፯ እና ፰ ላይ አንዳንዶቹ እንደ እርሱ ያላገቡ ቢሆኑ መልካም እንደሆነ ይናገራል ። (ቁጥር ፯ እና ፰ ይነበብ ።) ለእግዚአብሔር ሥራ ሲባል በብቸኝነት ቢቀር ምን ጥቅም ማስገኘት ይቻላል ? የቤተሰብ



ኃላፊነት የሌለበት ሰው ሙሉ ጊዜውን ለእግዚአብሔር ሥራ ማስረከብ ይችላል ። እርሱም ቤተሰብ ያላቸው ሰዎች ሊሄዱ ወደማይችሉበት ቦታ መሄድ ይችላል ። በገዛ ራሱ ጊዜ እርሱ እንደፈለገው መጠቀም ይችላል ፤ ስለሆነም በቤተሰብ ጉዳይ ጊዜ መውሰድ የለበትም ። አለማግባትም ከገቡት ይልቅ በቅድስና መኖር አይደለም ፤ ያላገባውም ሰውዬ ባለማግባቱ የበለጠ መንፈሳዊ እንደሆነም አይምሰለው ። አስፈላጊው ነገር ግን ስሜታችንን ከመከተል ይልቅ እግዚአብሔር ለሕይወታችን የወሰነልንን ማድረግ የበለጠ ጠቃሚ ነው ።

ያላገባ ሰው አንድ ዓይነት የተፈጥሮ ጉድለት እንዳለበት የተገመተበት ጊዜ ነበር ። ወይም ደግሞ አእምሮ የጎደለው ወይም ደግሞ በሌላ በኩል ስሜት እንደሌለው ይገመታል ። ይህ ግን እውነት አይደለም ። ማንኛውም ወጣት ለማግባት ወይም ላለማግባት በገዛ እጁ የመወሰን ኃላፊነት አለበት ። ሳያገቡ መቅረትም ነውር አይደለም ፤ ወይም ደግሞ እንደዚሁ ሳያገቡ መዘግየት ። ያም ሆነ ይህ አንድ ሰው የቤተሰብን ኃላፊነት መሸከም አልችልም በሚል ፍርሃት አለማግባትን መምረጥ የለበትም ።

በመንፈሳዊ ሕይወታቸው በቅድስና እስከኖሩ ድረስ ሴትም ብትሆን ወንድ በሕይወታቸው ዘመን ሁሉ በብቸኝነት ቢኖሩ አስነዋሪ አይደለም ። ጳውሎስ በ፩ኛ ጢሞቴዎስ ፭ ፡ ፳፪ ፦ «ራስህን በንጽሕና ጠብቅ» ይላል ። ለብዙዎች ሰዎች ማግባት የተሻለና መልካም ነገር ነው ። የተፈጥሮ ሥጋዊ ምኞትና የግብረ ሥጋ ፍላጎት በጣም ስለሚያይልባቸው ራሳቸውን መግታት አይችሉ ይሆናል ። ሆኖም ለወንድም ሆነ ለሴት በቀረው የሕይወት ዘመናቸው ሳያገቡ መኖር የሚቻል ነገር ነው ። በእግዚአብሔር ላይ ባላቸው እምነትና እርሱ በሚሰጣቸው ኃይል ብርታት በድንግልና መኖር ይችላሉ ። ብዙ ብቸኛ ሰዎች በዚህ ሕይወት ኖረው አሳይተዋል ። ኃይሉና ቃሉ ለማንኛውም ዘር ሰዎች እኩል ይሠራል ። ፈቃዱን እንዲያደርግ ለማንኛውም ሰው ኃይሉን ይሰጣል ።

አሁንም ቢሆን ጥቂት ያላገቡ ሰዎች አሉ ። እነር
ሱም ጌታን በተሻለ ሁናቴ ለማገልገል ብለው አይደለም ።
ነገር ግን የማግባት እድል ስላልገጠማቸው ነው ። ለዚህ
ምክንያቱ ምንድር ነው ? እነዚህ ሰዎች ያላገቡት እግዚ
አብሔር ስላልፈቀደ ነው ማለት እንችላለን ? (ውይይት ፡
ከወንዶች ይልቅ ብዙ ሴቶች ልጆች ያላገቡ ናቸው ።
በአንዳንድ ሀገር ባሕል ቤተሰቦች ለልጆቻቸው የሚያደ
ርጉት የጋብቻ ዝግጅት እየቀረ ነው ። ልጃገረዶች በሚ
ያገቡ ጊዜ የሚያገቡትውን ሰውዬ ጨርሰው አያውቁ
ትም ። በቁጥር ተመጣጣኝ የሆኑ ሴቶችና ወንዶች ሕፃ
ናቶች ቢወለዱም አንዳንዶችን ልጃገረዶች ሊያገቡ ይገባ
ቸው የነበሩ ወንዶች በየጦርነቱ ላይ ይሞታሉ ። ከዚ
ህም በቀር ከሴቶች ልጆች ይልቅ ለአቅመ አዳም ከመድ
ረሳቸው በፊት ብዙ ወንዶች ልጆች ይሞታሉ ። ከዚህ
የተነሳ ሴቶች ወንዶችን በብዛት ይበልጡአቸዋል ።)

አንድ ሰው የሚያገባው ወይም የማያገባው እግዚአ
ብሔር ስለ እርሱ ሕይወት የሚሰጠውን መመሪያ በመቀ
በል በግሉ የሚወስነው ጉዳይ ነው ። አንድ ብቸኛ ሰው
እግዚአብሔር በመራው በማንኛውም ሥራ ላይ ሆኖ
ክቡርና ጠቃሚ የሆነ ኑሮ መኖር ይችላል ። «ከዚህ
አስፈላጊ ከሆነ ከሕይወትህ ክፍል እግዚአብሔርን አታስ
ወጣው» የመጋቢ ደስታ ምክር ይህን የመሰለ ነበረ ።
ያለ እግዚአብሔር አመራር የሚደረግ ጋብቻ ሁሉ ፍጻ
ሜው ስለማያምር ሁከትና ችግር አለበት ። አስቀድሞ
የእግዚአብሔርን ፈቃድ ቢሻ ግን በእርግጥ የእግዚአብ
ሔርን ፈቃድ ሊያገኝ ይችላል ።

<u>ትምህርቱን በሥራ ላይ ማዋል</u> ፡—


ማሚቴ የተመለከተችው ትምህርትዋን ጨርሳ ሥራ
መያዝዋን ብቻ ነው ። አሁን ግን እግዚአብሔር ለሕይ
ወትዋ ያቀደላትን ነገር በቅድሚያ መፈጸሙ የበለጠ
አስፈላጊ ነገር እንደሆነ ተረዳች ። ስለዚህ አሁን የእግ
ዚአብሔር ፈቃድ ለእርስዋ ሕይወት ምን እንደሆነ ለመ
ሻት ቁርጥ ውሳኔ አደረገች ። እርስዋም እግዚአብሔር



ሕይወትዋን ለጋብቻ ወይም ላለማግባት ሆነ ዘግይታ እን
ድታገባ ቢፈቅድ እርሱ የፈቀደውን ሁሉ ለማድረግ
ቆረጠች ።

<u>ጸሎት</u> ፡— ያላገባህ ከሆንክ ጌታ የጋብቻህን አቅጣጫ
እንዲያሳይህ ፈቃዱን በጸሎት ጠይቀው ።

ከዚህም በቀር የማግባት እድል ስላልገጠማቸውና
ጨርሶ ላለማግባት ምርጫ ስላደረጉ ሰዎች ሁናቴ የበለጠ
ለመረዳት እንድንችል እግዚአብሔር አስተሳሰባችንን
ብሩህ እንዲያደርግልን በጸሎት እንጠይቀው ። ከግላዊ
ፍላጎትህ ይልቅ የእርሱ ፈቃድ ለሕይወትህ ምን እንደ
ሆነ እንድታውቅ እግዚአብሔር እንዲረዳህ ጠይቀው ።



የጥላሁንና የጽጌ ውይይት ስለ ጋብቻቸው ።

ክፍል ፪
ትምህርት ፩ — ፮
ለጋብቻ መዘጋጀት

የክፍሉ ዓላማ ፡— ቤተሰቦች ልጆቻቸውን ለጋብቻ እንዴት አድርገው ማዘጋጀት እንዳለባቸው ለማስረዳት ፣ ወጣቶች የኑሮ ጓደኛቸውን እንዴት እንደሚመርጡና ለጋብቻ ራሳቸውን እንዴት አድርገው ማዘጋጀት እንዳለባቸው መመሪያ ለመስጠት ።

የክፍሉ ጥቅስ ፡— ያዕቆብ ፭ ፡ ፫ — ፮

## ክፍል ፪ — ትምህርት ፩

## ማንን ላግባ ?

የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ፡— ዘፍጥረት ፳፬ ፡ ፳፭ — ፳፯

የቃል ጥናት ፡— ፪ኛ ቆሮንቶስ ፮ ፡ ፲፬ ና ፲፫ ለ

ዓላማ —.የኑሮ ጓደኛ እንዴት አድርጎ መምረጥ እንደሚቻል ለመርዳት፣
.አማኞችን ብቻ መርጠው እንዲያገቡ ለመምራት

መግቢያ ፡— የጽጌና የጥላሁን የትጭጭታቸው የደስታ ተካፋይ ይሆኑ ዘንድ አንድ ቀን እሁድ ከሰዓት በኋላ የቅርብ ጓደኞቻቸው በአቶ ኃይሌ ቤት ተሰበሰቡ ። እነርሱም ቡና እየጠጡና ቁርስ እየበሉ ሳሉ ተጋባዦቹ በደስታ በአንድነት ይጫዋወቱ ነበር ። ምክንያቱም ጊዜው በጣም ደስ የሚል ወቅት በመሆኑ ነው ። እነርሱም ጋብቻው መቼ መሆን እንዳለበት አልወሰኑም ነበር ። ነገር ግን በዚህን ጊዜ ሊያደርጉት የፈለጉት ደስ መሰኘታቸውን ከጓደኞቻቸው ጋር ለመከፋፈል ብቻ ነው ።

ተጋቢዎቹም መጋቢ ደስታ በየሳምንቱ ስለ ጋብቻ ያስተምሩ የነበረውን ክፍለ ጊዜ መካፈላቸውን ቀጠሉ ። እግዚአብሔር ስለ ጋብቻ የሚያስተምረውን ነገር ጥቅም አብዛኛዎቹ ሰዎች ስለተረዱ የትምህርቱ ተሳታፊዎች

ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ሄደ ። ከዚህም የተነሳ
ብዙ ቤተሰቦችና ወጣቶች ትምህርቱን ይከፈሉ ነበር ።
አንድ ቀን ምሽት መጋቢው ራሳቸውን እንዴት ለጋብቻ
እንደሚያዘጋጁ ልጆቻቸውም የኑሮ ጓደኛ እንዴት ሊመ
ረጥላቸው እንደሚገባ ለመረዳት ውይይት ከፈቱ ። መጋ
ቢውም ይህ ርዕስ ሦስቱን የትምህርት ጊዜ እንደሚሸፍ
ንና እነርሱም እያንዳንዱን ክፍለ ጊዜ እንዲከፈሉ አበረ
ታቱዋቸው ። የመጀመሪያው ትምህርት ማንን ማግባት
እንደሚገባ መመሪያ ይሰጣል ።

ትምህርት ፡— ጋብቻ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ዋነኛውን
ቦታ የያዘና የተቀደሰ ነው ። በቤተሰብና
በሕብረተሰብ መካከል ከሚፈጸሙ ነገሮች ዋነኛው ነገር
ነው ። «በጋብቻው ጊዜ ያልጋበዘኝ ሰው በቀብሩም
እለት አያገኘኝም» ይህ አባባል በአንዳንድ ሀገር ሕብረ
ተሰብ መካከል ጋብቻ ከፍተኛ ሥፍራ እንደያዘ ያሳስበ
ናል ። ነገሩም በጣም ቤተሰባዊ የሆነ ጉዳይ ነው ።
በመጽሐፍ ቅዱስ ዘመን ለልጆቻቸው ባልና ሚስት የሚ
ፈልጉትና ዝግጅቱንም የሚጨርሱት ቤተሰቦች ነበሩ ።
በአንዳንድ በኢትዮጵያ ክፍለ ሀገራትም በዚህ ባሕል
እየተጠቀሙበት ነው ። በዚህ በኩል በማይጠቀሙበት
ሥፍራ ቢሆን እንኳ ልጆች ከማግባታቸው በፊት የቤተ
ሰቦቻቸውን ምክርና ፈቃድ መጠየቅ ይኖርባቸዋል ።
ቤተሰቦቻቸውም በጋብቻ ጉዳይ ላይ ልጆቻቸውን ለማዘ
ጋጀት እንዲችሉ በጥበብ ማሰብና የልጆቻቸውን ዝንባሌ
በፍጥነት የሚረዱ መሆን አለባቸው ።

ስለ ጋብቻ በምንወያይበት ጊዜ ብዙ ጥያቄዎች ወደ
አእምሮአችን ይመጣሉ ። ጋብቻን በሚያስቡ ሰዎች
አእምሮ የሚቀረጸው ከፍተኛው ጥያቄ ፡— «የማገባውን
ወይም የማገባትን እንዴት ማወቅ እችላለሁ ?» የሚል
ነው ።

ይህ ጥያቄ ሊያገባት ወይም ልታገባው የማይገባውን
ሰው በማመልከት መልሱ በሚገባ ሊመለስ ይቻላል ።
(፪ኛ ቆሮንቶስ ፮ ፣ ፲፬ ፣ ፲፰ አንብብ ።) በዚህ ላይ ክርስ



ቲያን ወጣት ያላመነችይቱን ማግባት እንደሌለበት በግ
ልጥ ያስረዳል ። በሌላ ሥፍራ ደግሞ ፡— «ሁለት ሰዎች
ሳይስማሙ እንዴት በአንድነት ይሄዳሉ ?» ይላል ።
(አሞጽ ፫ ፣ ፫) በሌላ ሥፍራ ደግሞ ፡— «ቤትም እርስ
በርሱ ከተለያየ ያ ቤት ሊቆም አይችልም» የሚል እናገ
ኛለን ። (ማርቆስ ፫ ፣ ፳፭) ሁለቱም ተጋቢዎች በክርስ
ቶስ ካልተጣመሩ በቤታቸው ግጭት ይፈጠራል ፣ ሊስማ
ሙም አይችሉም ። ያም ቤት የተከፋፈለ ቤት ይሆናል ።

ሰውዬው የቤተ ክርስቲያን አምልኮ ተሳታፊ መሆኑ
ለአማኝነቱ ማረጋገጫ አይደለም ። ስለዚህ ከቃል ኪዳን
በፊት እያንዳንዳቸው አማኝ መሆናቸውን ለማረጋገጥ
መጠናናት ይኖርባቸዋል ። አንደኛው ሌላኛው ክርስቲ
ያን እንደሆነ በምን ሁናቴ ማረጋገጥ ይችላል ? (ማቴዎስ
፯ ፣ ፳ አንብብ ።) ክርስቲያን የክርስቶስን ፍሬ የያዘ
ነው ። የክርስቲያን ሕይወት ፍሬዎች የአማኝነቱ ማረጋ
ገጫዎች ናቸው ።

ወጣት ክርስቲያኖች ከበሰሉትና ከቆዩት ጋር ተመሰ
ጣጥረው ሕብረት ቢያደርጉ በጣም ይጠቅማል ። በዚህ
መንገድ ተመሳሳይ አሳማና ግብ ለሕይወታቸው ያላቸውን
ሰዎች ማግኘት ይችላሉ ። ከቀድሞ ጊዜ ጀምሮ እግዚአ
ብሔር ሴቶችና ወንዶች ወጣቶችን ወደ ጋብቻ እየመራ
ቸው ነው ። የተለያየ ጾታ ያላቸው ሰዎች እርስ በርስ
የሚሳሳቡ የተፈጥሮ ባሕሪይ አላቸው ። ወጣቶች አብ
ረው ተደባልቀው ጥቂት እንደቆዩ ጠሊቅ የሆነ ወዳጅ
ነት በጥቂቶቹ ውስጥ ይመሰረታል ። በተለይ በዚህን
ጊዜ እግዚአብሔር በዚህ ወዳጅነት ውስጥ እንዲመራና
የእርሱ ፈቃድ ያልሆነ ጓደኝነትን ደግሞ እንዲያቋርጥ
መጸለይ ይገባል ። ጋብቻ አጥጋቢ ውጤት የሚኖረው
አብዛኛውን ጊዜ ተጋቢዎቹ ከአንድ ዓይነት ባህልና
የኑሮ ሁናቴ የመጡ እንደሆን ነው ።

ወጣቶች የማያከብሩትን ሴት ወይም ወንድ ማግባት
የለባቸውም ፣ ምክንያቱም ያለአክብሮት ፍቅር ሊኖር
አይችልም ። ስለ ጋብቻ ጉዳይ በምንጸልይበት ጊዜ ጌታ

እንደተስፋ ቃሉ ግልጽ የሆነ መመሪያ ይሰጠናል ። ለዚህኛው ክፍል የተሰጠንን የቃል ጥናት ጥቅሳችንን በአንድነት እንበለሰው ። (ያዕቆብ ፩ ፥ ፭ — ፮) ጋብቻ በጌታ ውስጥ ብቻ ሲሆን በጣም አስፈላጊ ይሆናል ። ዮሴፍና ማርያም በነበራቸው ቅድስናና የጸሎት ሕይወት አንዳቸው ለሌላቸው ሊሰጡ ችለዋል ። እነርሱም በጌታ በይጣመሩ ኖሮ የገጠማቸውን ፈተና ሊወጡት የሚቻል አልነበረም ። እግዚአብሔር የመረጠላቸውን የኑሮ ጓደኛ ለማግኘት እያንዳንዳቸው ተጋቢዎች ብዙ ፈተና ሳይገጥማቸው አልቀረም ።

ተጋቢዎቹ በሕብረትም ሆነ በግል ሲጸልዩ እግዚአብሔር ስለ አንድነታቸው ያለውን አመራር ለማወቅ መፈለግ አለባቸው ። በዚህ ጉዳይ ላይ ከቤተሰቦቻቸው ጋርም መጸለይ አለባቸው ። ይህን አስፈላጊ ውሳኔ በሚወስኑበት ጊዜ ከልጆቻቸው ጋር ሆነው እግዚአብሔር ፈቃዱን እንዲያሳያቸው ቤተሰቦች አብረው ሊጸልዩ ይገባል ። (ምሳሌ ፫ ፥ ፭ — ፮ ይነበብ ።)

<u>ትምህርቱን በሥራ ላይ ማዋል</u> ፦

ጉዳዩ የበለጠ ሊታሰብበት የሚገባ ነገር በመሆኑ ጥሳሁን አንዳንድ ጥቅሶችን በማስታወሻ ላይ ይጽፍ ጀመር ።ከዚያም ከጽጌ ጋር የጻፈውን አብረው አነበቡት ። ከዚህም ሕይወታቸውን በአንድነት ስለመሩና አንዳቸው ለሌላው ፍቅር እንዲኖራቸው ስላደረገ እግዚአብሔርን አመሰገኑት ።

የእግዚአብሔርን ቃል በመመልከት ፤ ልጆቻችሁ ስለሚኖራቸው የጓደኝነት ሕይውት ፈቃዱን እንዲያሳያችሁ ጠይቃችሁት ታውቃላችሁን ? ልጆቻችሁ እስከ አሁን ገና ሕፃናቶች ከሆኑ በርሱ እንዲደስቱ ጸልዩላቸው ። በአደጉም ጊዜ ጌታን ከሚወዱት በቀር ከማንም የጋብቻ ፍቅር እንዳኖራቸው ጸልዩላቸው ።

<u>ጸሎት</u> ፦ ወላጆች ፤ ልጆቻችሁ ገና በብላቴንነት ዘመናቸው ወደ ትክክለኛ ጓደኛ እንዲመራቸው ጌታን ጠይቁላቸው ።



ያላገባችሁ ወጣቶች ደግሞ እግዚአብሔር ልታገቡትና ልታገቢት ወደሚፈልጋችሁ ሰው እንዲመራችሁ ጸልዩ ። ጓደኝነታችሁንም እርሱ እንዲመራና እንዲቆጣጠር ጠይቁት ።

## ክፍል ፪ — ትምህርት ፭

# መቼ ማግባት ይሻለኛል

<u>የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል</u> ፦ መዝሙር ፻፳፯ (፻፳፮) ፥ ፫ — ፭ ፤ ምሳሌ ፫ ፥ ፭ — ፮

<u>የቃል ጥናት</u> ፦ መዝሙር ፻፳፯ (፻፳፮) ፥ ፩ — ፭

<u>ዓላማ</u> — ወጣቶች የሚያገቡበትን ጊዜ በገዛ እጃቸው ከመወሰናቸው በፊት የእግዚአብሔርን አመራር እንዲጠብቁ ለማበረታታት ፣

እያንዳንዱን ውሳኔአቸውን ለእርሱ አደራ እንዲሰጡት ለማድረግ

<u>መግቢያ</u> ፦ ጽጌ ሃያ አንድ ዓመት ሊሆናት ተቃርቧታል ። «እድሜዬ ለአቅመ ሄዋን ደርሶአል» አለች ። «ጥላሁንንም አጥብቄ ስለምወደው ላገባው እፈልጋለሁ ። ነገር ግን ወደ ነርስ ትምህርት ቤት ተመልሼም አስቀድሜ የነርስነት ትምህርቴን ማጠናቀቅ ይኖርብኝ ይሆን እንዴ ? ብዬም አስባለሁ ። ወይንም ደግሞ የሂሳብ አያያዝ ትምህርት ልማር ይሆን ? ወይስ ታይፕ ላጥና ?» የሚሉ ብዙ ሃሳቦች ወደ አእምሮዋ መጡ ።

«ጋብቻ ለሕይወት አስፈላጊ የሆነ ይህን የሚመስል ቁም ነገር ነው ። እኔም የእግዚአብሔርን አመራር ለመከተል ብዙ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርብኛል» ብላ በሚስጢር ለጓደኛዋ ለማሚቴ ነገረቻት ። መጋቢ ደስታ በሚቀጥለው ትምህርታቸው ለጋብቻ መዘጋጀት በሚል ርዕስ ስለሚናገሩ ጊዜውን በጉጉት ትጠብቅ ጀመር ።

<u>ትምህርት</u> ፦ መጋቢ ደስታም ሊያቀርቡ ያሉት ትምህርት ርዕስ በጣም አስፈላጊ እንደሆነ ተገንዝበዋል ። እርሳቸውም እንዱ ለጋብቻ መልካም የሚሆ

ንለት የእድሜ ዘመኑ ለሌላው እንደማይሠራ ያውቁ ነበር። እርሳቸውም በዚህ ጉዳይ ማንኛውም ወጣት እንዲሰናከል አይፈልጉም። መጋቢውም ሃሳባቸውንና ቃላቸውን እርሱ እንደሚያስበው አድርጎ እንዲመራላቸው እንደገና ጌታን ጠየቁት።

ወንድ ሲያገባ የስንት ዓመት እድሜ ሰው ቢሆን መልካም ነው? ልጃገረድዋስ የስንት ዓመት ትሁን? (ተወያዩበት።)

«ከሀገር ወደ ሀገር የሰዎች ባሕል የተለያየ ስለሆነ ይሄኛው የእድሜ ዘመን ለጋብቻ መልካም ነው ብሎ ለመወሰን አስቸጋሪ ነው» በማለት ንግግራቸውን ጀመሩ። አንድ ሰው ለሕብረተሰቡ የሚጠቀመውን ነገር በማሰብ በአእምሮም ሆነ በሰውነቱ ሲዳብር ያን ጊዜ ለጋብቻ ብቁ ስለሆነ በዚህን ጊዜ ለጋብቻ ዝግጁ መሆኑ መልካም ነው። ከጋብቻ በፊት የነበሩ ዓመታት በአካልም ሆነ በወኔ እንዲሁም በመንፈሳዊ ሕይወት የሚዳብሩበት ጊዜ ነው።

አንድ ወጣት ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን መንፈሳዊ ግንኙነት በሚገባ ያዳበረ እንደሆነ አቋሙ የበለጠ ለጋብቻ ብቁ እንዲሆን ወደሚያደርሰው ደረጃ ያመጣዋል። እርሱም እንዴት መጸለይ እንደሚገባና እንዴት የእግዚአብሔርን ቃል ማጥናት እንዳለበት እንዲሁም እንዴት መመስከር እንዳለበት መማር ይገባዋል። ይኸም ለማንኛውም ቤት አስፈላጊና ጠቃሚ የሆነ ነገር ነው። በተለይም አዲስ ለተቋቋመ ጥናት መልካም ነው። በተለይ ተጋቢዎቹ በክርስቶስ የተጣመሩ ከሆነ ምኞታቸው የጌታ ፈቃድ በሕይወታቸው እንዲፈጸም ነው። እንዳንድ ሰዎች በአሥራ ስምንት ዓመታቸው ለጋብቻ የተዘጋጁ ሲሆኑ አንዳንዶቹ ደግሞ ሰላሳ ዓመት በሞላቸው ጊዜ እንኳ አይዘጋጁም።

ተጋቢዎቹም በተቀዳሚ ባል ወይም ሚስት ማለት ምን ማለት እንደሆነ የተማሩና ቤተሰብን የማቋቋም ኃላፊነት የተረዱ እንዲሁም ቤተሰብን ለማቋቋም የተዘጋጁ



መሆን አለባቸው። እነርሱም ጋብቻ ያመጣውን ለውጥ ለመቀበል የተዘጋጁ መሆን ይኖርባቸዋል። ከዚህም በቀር ከመጣው ለውጥ ጋር ራሳቸውን ለማዛመድ የሚያስችል ችሎታ ሊኖራቸው ይገባል። ከመጋባታቸውም አስቀድሞ ቤታቸውን የሚያደራጁበት ገቢ ሊኖራቸው ይገባል። እግዚአብሔር እንዳለው እያንዳንዳቸው እናት አባቶቻቸውን ትተው ለመጣመር ከታዘዙ ከላይ በዝርዝር የቀረቡት ነገሮች ያስፈልጉዋቸዋል።

ከጋብቻ በፊት ያሉት ዓመታት ጠባይን የማዳበሪያ ጊዜአቶች ናቸው። አብዛኛውን ጊዜ እግዚአብሔር እያንዳንዱን ግለሰብ የሚያሳድገው በመከራ ውስጥ ነው። ጠባይም እያደገና እየዳበረ የሚሄደው ለእነዚህ ችግሮች መፍትሄ ለመፈለግ በሚደረጉ ትግሎች ውስጥ ነው። ከልጅነት ወደ ጋብቻ ቀጥታ መሄድ እያንዳንዱ ሰው የግል ችግሩን ታግሎ መፍትሄ የመፈለግ ትምህርት እንዳያገኝ ይከለክለዋል። ጋብቻ ከተመሰረተ በኋላ የግል ችግራቸውን በራሳቸው ጥረት እንዲወጡት ለተጋቢዎቹ እነሆ ተወጡት ተብሎ ይሰጣቸዋል እንጂ ለቤተሰቦቻቸው አይሰጥም። ለችግራቸው መፍትሄ የሚያገኙት የራሳቸውን ችግር ለመወጣት በሚያደርጉት የትግል ልምምድ ውስጥ ነው። ለራሳቸው ችግር መፍትሄ ለማግኘት ያልተሰናዱ ከሆነ ገና ለጋብቻ አልተዘጋጁም ማለት ነው።

«ከጋብቻ በፊት ትምህርትን መጨረስ ይገባል ወይስ ከጋብቻ በኋላ ወደ ትምህርት መሄድ የሚቻል ነው?» ይህ ጥያቄ ከነበሩት ሰዎች በአንደኛው ተጠየቀ። (ተወያዩበት።)

የሚቻል ከሆነ ከጋብቻ በፊት ትምህርትን መጨረስ መልካም ነው በማለት መጋቢ ደስታ ምክራቸውን ለገሡ። ጋብቻ በራሱ ብዙ መስተካከልን የሚጠይቅ ነገር ነው። አንዳንድ ጊዜ ጎልማሶች የማታ ትምህርት እየተማሩ ቀን መሥራት ስላለባቸው በሥራ ላይ ተሰማርተው ይውላሉ። ስለዚህ አብዛኛውን የቀኑንና የምሽቱን

ጊዜ ከሚስቱ ተለይቶ ይውላል። ተጋቢዎቹ አብዛኛውን ጊዜ አብረው የሚሆኑት ማታ ሲሆን ነው። ወጣትዋ ሚስትም ዘመዶችዋ ወይም ጓደኞችዋ በቅርብ ካልኖሩ ቀኑን ሙሉ ያለ ሰው ስትውል ብቸኝነት ይሰማታል። ወይም ደግሞ የቤትዋን ኃላፊነት ቸል በማለት የትምህርት ቤትዋ ሥራ ሸክም ይሆንባት ይሆናል። ይሄ በተለይ በእርግጥ ሸክም የሚሆንባት ሕፃናቶች በቤት ካሉና የእናታቸው ጥንቃቄና እርዳታ በሚያስፈልጋቸው ጊዜ ነው።

ከዚህም በስተቀር መጋቢ ደስታ በሥራ ላይ እያሉ መማር ስለሚያስከትለው ሌላ ችግር ጠቁመዋል። «አንድ ተማሪ ከትምህርቱ ብዙ ጥቅም ማግኘት እንዲችል ብዙ ማጥናት አለበት። ነገር ግን በቤት በሚሆንበት ጊዜ ደግሞ ብዙው ሰዓት ለጥናት ስለሚውል ከቤተሰብ ጋር የሚሆኑበትና አብረው የሚነጋገሩበት ጊዜ በጣም አጭር ይሆናል።»

«ጥቂት ኃላፊነት ብቻ ሲኖርብን ለማጥናትና ከክፍል ሥራ ጥቅም ማግኘት ቀላል ነው። ከጋብቻ በኋላ ትምህርትን መቀጠል የማይቻል ነገር አይደለም» በማለት ንግግራቸውን በመቀጠል ፦ «ሆኖም እያንዳንዳቸው ተጋቢዎች በግላቸው የሚበጀውን ነገር ይወስናሉ። በዚህ ላይ የጋብቻን ቅንብር ከትምህርት ቅንብር ጋር አጣምረው ለመምራት ይቻላቸው እንደሁ መወሰኑ የተጋቢዎቹ ኃላፊነት ነው። መልካም ጋብቻ ዝም ብሎ በጋጣሚ የሚሆን ነገር አይደለም። እያንዳንዳቸው የእርሱንና የእርስዋን ድርሻ በማዋጣት ለጋብቻቸው የሚያበረክቱት ነገር ነው። እያንዳንዳቸው ጋብቻቸው በሚገባ የተዋጣ እንዲሆን ሊናፍቁና ትጋት ሊያሳዩ ይገባል።»

«ምናልባት ከተጋቢዎቹ አንዳቸው ውጭ ሀገር ሄዶ የመማር እድል ቢገጥመውና ሁለቱም በአንድ ላይ መሄድ የማይችሉ ከሆነ ባልና ሚስት ተለያይተው እንዲኖሩ የእግዚአብሔር ፈቃድ አይደለም። ስለዚህ አብረው የመሆናቸው ጉዳይ ጨርሶ የማይቻል ከሆነ እግዚአብ



ሔር በዚህ ነገር ምክንያት መለያየታቸውን እንደፈቀደ እርግጠኛ ይሁኑ። ከሁለቱ አንዳቸው ባሕሉና የኑሮው ሁናቴ ቀድሞ ከነበረበት ስፍራ ፍጹም ልዩ ስለሚሆን ተመልሶ ሲመጣ የቀድሞው እንግዳ ስለሚሆንበትና ስለማይጥመው ሌላ ዓይነት አለመግባባትና ችግር ይፈጠራል። ወደ ውጭ ሄዶ የነበረው አዲስና እንግዳ የሆነ ባሕል ስለተማረ በመካከላቸው እንደደንቃራ ቆሞ ሊያሻሽሉት የማይችሉትን ጠንቅ የሚፈጥርባቸውና ወደ መለያየት የሚያደርሳቸው ሊሆን ይችላል።»

በመጨረሻም ፦ «ትምህርት መልካምና ጠቃሚ ነገር ነው። ቢሆንም ትምህርት አምላካችን መሆን የለበትም» አሉ። «ከዚህ ሁሉ ይበልጣል የምንለውን ትምህርት በመቀጠል ትዳራችንን የሚያፈርስብን ከሆነ አነስተኛ ነው ብለን የምንገምተውን መተው ነው።»

ትምህርቱን በሥራ ላይ ማዋል ፦

ጽጌ ጥላሁን የአሥራ ሁለተኛ ክፍል ትምህርቱን ያጠናቀቀና ለቤታቸው መተዳደርያ በቂ የሆን ደሞዝ የሚያስገኝ ሥራ ስላለው ደስ አላት። የሚቻል ከሆነ ለሥራው ማዳበርያ ይጠቅመው እንደሆን ወደ ትምህርት ቤት ተመልሶ ሊማር እንደሚወድ ታውቃለች። መወሰን ስላለባቸው ነገሮች መጸለይ በእነርሱ ዘንድ ልክ እንደ ተለመደ ነገር ሆኖአል። ሊወስኑዋቸው የሚገባቸው ነገሮች እጅግ ብዙ ስለሆኑ እግዚአብሔር በነገር ሁሉ ለእርዳታ እንዲተባበራቸውና ሊያደርጉ ያሉትን እንዳቀነባበረላቸው አወቁ። ችግራቸውን ሁሉ ወደ ጌታ እያቀረቡ ሲጸልዩ ለመንፈሳዊ እድገታቸው ብዙ እረድቶአቸዋል። የየግል ጉጉታቸውን በተከፋፈሉ ቁጥር አንዳቸው ወደ ሌላቸው ይበልጥ እየተቀራረቡ ሄዱ።

በዚህን ጊዜ ሁለቱም በመጀመሪያው የጋብቻ አመታቸው በየግላቸው የሚፈለግባቸውን የቤተሰብ ኃላፊነት ለመጠበቅ ስለተሰማቸው ራሳቸውን አሳልፈው ለመስጠት ቃል ኪዳን ገቡ። አሁን እያደረጉ እንዳሉት ሁለቱም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በአንድነት ይሠራሉ።

በመጀመሪያው ዓመት ቅንብር ላይ ጽጌ ራስዋን ለጋብቻ ዋና ለቤትዋ ቅዱስ ስጦታ አድርጋ ለማስረከብ ፈቃደኛ ሆነች ።

ጸሎት ፦ ወደፊት ስለ ጋብቻችሁ በአንክሮ የምትመለከቱ ሰዎች ጌታ ለእናንተ ያለውን ትክክለኛ የጋብቻ ጊዜ እንዲያሳያችሁ ጠይቁት ።

ቤተሰቦችም በዚህ ጉዳይ ላይ ልጆቻችሁን መምከር እንድትችሉ ጥበብ እንዲሰጣችሁ ጠይቁት ።

ክፍል ፪ — ትምህርት ፯

## የእጮኝነት ጊዜ

<u>የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል</u> ፦ ዘፍጥረት ፳፬ ፡ ፱ — ፷

<u>የቃል ጥናት</u> ፦ ፪ኛ ጴጥሮስ ፫ ፡ ፲፫

<u>ዓላማ</u> — •የእጮኝነትን ጊዜ ዓላማ ለማመልከት፣
ወጣቶችም ከማግባታቸው በፊት ወደ አቅመ አዳም ደረጃ እንዲደርሱ ለመምከር

<u>መግቢያ</u> ፦ «ጋብቻችን ከመድረሱ በፊት የቃል ኪዳናችን ወቅት እስከመቼ ይቀጥላል ?» በጥላሁንና በጽጌ አእምሮ ውስጥ ከቀረው ጎላ ብሎ የሚጉላላው ጥያቄ ይህ ነበር ። የጥላሁን ወላጆች በሌላ ክፍለ ሀገር ይኖሩ ስለነበር ጥላሁን ጽጌን ለጋብቻ እንዳጬት ጻፈላቸው ። እርሱም በደብዳቤው ስለ ጽጌ ቤተሰቦችና አምልኮት ይከፈሉበት ስለነበረው ጸሎት ቤት እንዲሁም መጋቢ ደስታ በጋብቻቸው ጉዳይ እንደረዱዋቸው አትቶ ነበር ። እነርሱም ጌታ ልጃቸውን የመራበትን መንገድ በማድነቅ ደስ ከተሰኙ በኋላ በጋብቻው ተስማሙ ። የጋብቻቸው ወቅት በእርሻ ላይ በማይሆኑበት ጊዜ ከሆነ ለመምጣት ደስ እንደሚላቸውም ተናግረዋል ።

ከጋብቻው አስቀድሞ የጋብቻው ቀን እንደሚያመች ሆኖ መታቀድ እንዳለበት ስለወጠኑ በዚህ ጉዳይ ላይ መጋቢ ደስታ እንደሚረዱዋቸው ተስፋ ያደርጋሉ ።



ክፍል ፫
ትምህርት ፰ — ፲
በልምምድ የሚገለጥ የጋብቻ ግብር

<u>የክፍሉ ዓላማ</u> ፦ መመሪያ ለመስጠትና እርምጃ የሚወሰድበት ግብ ምን እንደሆነ በማስረዳት ወጣቶች የራሳቸውን ኃላፊነት ተረድተው ራሳቸውን እንዲያዘጋጁ ለማድረግ ነው ። ከዚህም በቀር የተጋቡት ደግሞ በጋብቻ ዓለም ውስጥ የሚገጥማቸውን ነገር እንደ አመጣጡ ለመወሰንና የሚገጥማቸውን ችግር ለማረም እንዲችሉ ለማድረግ ነው ።

<u>የክፍሉ ጥቅስ</u> ፦ ፊልጵስዩስ ፪ ፡ ፫

ክፍል ፫ — ትምህርት ፰

## ፍቅር ፡ መግባባትና መተማመን

<u>የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል</u> ፦ ፩ኛ ቆሮንቶስ ፲፫

<u>የቃል ጥናት</u> ፦ መኃሊ ፰ ፡ ፯

<u>ዓላማ</u> —•የፍቅርን አብሮ የመኖርንና የታማኝነትን አስፈላጊነት ለማሳየት፣
•ተጋቢዎቹ አንዳቸው ለሌላቸው ያላቸውን ፍቅር በሥራ እንዲገልጡ ለመምራት

<u>መግቢያ</u> ፦ ጽጌ ስለ አዲሱ ጋብቻዋ መቃረብ ልቧ ነጋሪት ቢመታም ለጥላሁን ባላት ፍቅርና የእርስዋ ስለሚሆነው ደስታ ኃሴት ታደርግ ነበር ። እርስዋም በሚስትነትዋ ልትቀበለው ያላትን ኃላፊነት ስለምታውቅ ሕይወትዋ ዘወትር የተፍታታ ነፃነት እንደማይኖረው ይገባታል ። ጋብቻ ብዙ ኃላፊነትን የሚጠይቅ ነገር ነው ። እርስዋም አንዳንድ ጊዜ ቤተሰቦችዋ በክፍላቸው ውስጥ ሆነው በማንሾካሾክ የቤተሰብ ኃላፊነት ምን ዓይነት ከባድና አስቸጋሪ እንደሆነ ሲነጋገሩ ትሰማ ነበር ። ይህ በመሆኑ ገና እርስዋ ያልተለማመደችው ኃላፊነት እንደሚጠብቃትና ዋስትና ያለውን የአባትዋን ቤት ለቃ

ነው። ይሄም ደግሞ ክቡር ነው። ቢሆንም በዚህ ጉዳይ ላይ ችግር ከገጠማቸው ከጋብቻ በፊት በግብረ ሥጋ ኃጢአት ላይ እንዳይወድቁና ጌታን እንዳያሳዝኑ መፍትሄ ቢፈለግለት መልካም ነው። ወደ እርሱ ባቀረ ቡአቸው ጊዜ ጌታ ችግሮቹንና ፈተናውን ያውቃል። ስለዚህ ተጋቢዎቹን እርሱን ወደሚያስከብር መፍትሄ ይመራቸዋል።

ጋብቻ የተቀደሰ ሥርአትና የተለየ ቁም ነገር የሆነ ቅዱስ መሰጠት ነው። ይኸንንም እርምጃ ያለ ጸሎትና ዝግጅት ልንወስደው አይገባም። የቃል ኪዳኑ ጊዜ እግዚአብሔር ለዚህ ዝግጅት የሚሰጠን ወቅት ነው። በእነዚህ ጊዜአት ውስጥ ተጋቢዎቹ በሕይወታ ቸው ብስለትን በማግኘት ይኸንን ኃላፊነት ለመቀበል የማይችሉ ከሆነ የእግዚአብሔርን ፈቃድ እስኪያረጋግጡ ድረስ ቢያዘገዩት አይከፋም። የቃል ኪዳኑ ጊዜ ተጋቢ ዎቹ አንዳቸው ለሌላቸው በመኃላ የሚሰጣጡበት ወቅት ነው። ምናልባት ጥቂት አለመግባባት ቢኖር ከጋብቻ በኋላ ይስተካከላል ብሎ ዘው ብሎ ገብቶ በኋላ ችግር ውስጥ ከመግባት ይልቅ ጨርሶ መተው ይሻላል። የእግዚአብሔር ፈቃድ ስለመሆኑ እርግጠኛ ባይሆኑና ቢጠራጠሩ ጠብቆ ማረጋገጡ መልካም ነው። በጥርጣሬ የተመሠረተ ጋብቻ ደስተኛና ዘላቂነት ያለው መሆኑ የመነመነ ነው።

እግዚአብሔር ተጋቢዎቹን በሚያቀራርባቸው ጊዜ ወላጆች መሰናክል መሆን የለባቸውም። ከልባቸው የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚሹትን ተፈላላጊዎችንና ወላጆቻቸውን እግዚአብሔር ይመራቸዋል። ልጆቻቸው ለሕይወታቸው ታላላቅ ውሳኔዎችን ለማድረግ ብቁአን እንዲሆኑ ወላጆቻቸው የማበረታታት ኃላፊነት አለባ ቸው።

<u>ትምህርቱን በሥራ ላይ ማዋል</u> ፦

ጽጌና ጥላሁን መጋቢ ደስታ ከመጋባታቸው በፊት በእጮኛነት ምን ያህል ጊዜ መቆየት እንደሚኖርባቸው



ይጠቁሙናል ብለው ተስፋ አድርገው ነበር። ቢሆንም በእጮኛነት ምን ያህል ጊዜ መቆየት እንደሚገባ የተወ ሰነ ጊዜ እንዳልተደነገገ ተገነዘቡ። ይህ ራሳቸው የሚወ ስኑት ጉዳይ ነው። የመጋቢ ደስታ ዓላማ የሚወስኑት ነገር በሚኖራቸው ጊዜ እግዚአብሔር ለእነርሱ ያለውን ፈቃድ መፈለግ እንዲማሩ መምራት ብቻ ነው።

እነርሱም ከመጋባታቸው በፊት ማድረግ ስላለባቸው ነገሮች እያሰቡ ነበር። ጽጌም ገና ሊመሠርቱት ላለው ቤታቸው የሚሆን አንዳንድ ነገር ለመሥራት ስላቀደች ጓደኛዋ ኤልሳቤጥ ስፌት እንድታስተምራት ጠየቀቻት። እርስዋም ይኸንን ሞያ ብታጠና ለወደፊቱ እንደሚጠቅ ማት ታውቅ ነበር። ጥላሁንም መሥሪያ ቤቱ በጊዜ እንዳይደርስ ችግር የማይፈጥርበትን በአቅራብያው ቤት ይፈልግ ጀመር። እርሱም የጋብቻቸው ቀን እንደተቃረበ የዓመት ፈቃዱን ይጠይቃል።

እነርሱም ከመጋባታቸው በፊት የሚጠናቀቁትን ነገሮች ሊያከናውኑ ይሻሉ። የጥላሁን ቤተሰቦች በዚያን ጊዜ ለመገኘት ከቻሉ ጋብቻቸው በስድስት ወር ጊዜአት ውስጥ ይፈጸማል።

<u>ጸሎት</u> ፦ በጋብቻ ላይ ያላችሁ ቤተሰቦች ደግሞ እግዚ
አብሔር ልጆቻችሁንና የጋብቻን ነገር በቁም ነገር የሚመለከቱትን ወጣቶች ትረዱዋቸው ዘንድ ብቁ አን እንዲያደርጋችሁ እግዚአብሔርን ጠይቁት።

ወጣቶች ደግሞ እግዚአብሔር በሁሉ ነገር ማስተዋ ልና ብስለትን ይሰጣችሁ ዘንድ ጠይቁት።

ስለ ገንዘብ ጉዳይም ቢሆን መግባባት በሚችሉት ውሳኔ ላይ መድረስ አለባቸው ። ይህ ትምህርት እጅግ በጣም አስፈላጊ ስለሆነ በሚከተለው ትምህርት ላይ በሚገባ ማብራርያ ይሰጥበታል ።

መደጋገፍ ታማኝነት የቤተሰብ አጠቃላዩና ዋነኛው ግብ መሆን ይገባዋል ። ማንም ሰው ቢሆን በአካባቢው ስለ ኑሮ ጓደኛው ወይም ጓደኛዋ ክፉ ነገር ሲነገር ሰምቶ ወይም ሰምታ ደስ የምትሰኝ ወይም የሚሰኝ ሰው አይኖርም ። በእያንዳንዱ ባልና ሚስት መካከል አንዳንድ አለመግባባት ሊፈጠር ይችላል ። ነገር ግን ነገሩ በጌታና በእነርሱ መካከል ብቻ መቅረት አለበት ። ያልተግባቡበት ነገር ወሬው ከቤታቸው መዝጊያ ውጭ መውጣት የለበትም ። ስለ ባልዋ ክፋነት ለዘመዶችዋ የምታወራሴት ስለራስዋ ጨርሳ የማታስብ ናት ። ባልዋም እርስዋን ለሚስትነት በመረጣት ጊዜ እንዲያው በዘፈቀደ ነው እንጂ በማስተዋል እንዳልሆነ መናገርዋ ነው ። ባልና ሚስቶች አንዳቸው ለሌላቸው ባደረጉት መኃላ መሠረት አንዳቸው ለሌላቸው ተደጋጋፊዎችና ታማኞች እንዲሆኑ እግዚአብሔር ይፈልግባቸዋል ። ይኸም ታማኝነት በሕመምና በድኅነት እንዲሁም በጤንነትና በብልጽግናም ጊዜ የሚኖር ነው ። ክርስቲያን ባልና ሚስቶች እያደገ የሚሄድ ፍቅርና እርስ በርስ መደጋገፍ ሊኖራቸው ይገባል ። እነርሱም ከኑሮ ጓደኛቸው ጋር በቀር ከሌላ ከተቃራኒ ጾታ ጋር የቀረበና የውስጥ ሚስጢራዊ አንድነት ሊኖራቸው አይገባም ።

<u>ትምህርቱን በሥራ ላይ ማዋል</u> ፦

ፍቅርና እርህራሄ መግባባትና ተደጋጋፊነት እንዲሁም ታማኝነት እነዚህ ታላላቆቹ የጋብቻ ሁሉ ግቦች ናቸው ። ጥላሁንና ጽጌ እርስ በርሳቸው ለነበራቸው ፍቅር እርግጠኞች ነበሩ ። እነርሱም ቤተሰብ እንዲኖራቸው ስለመፈለጋቸው ጉዳይ መወያየትና መጸለይ እንዳለባቸው ያውቃሉ ። እነርሱ ቀድሞውኑ የአንድ ቤተ ክርስቲያን አባላት ስለሆኑ ይሄ ችግር አይፈጥርባቸውም ።



ትምህርት ፦ ከጋብቻ በፊት ያሉት ወራቶች የበለጠ የመተዋወቂያና በመቀራረብ ፍቅርን የማዳበርያ ወቅት ናቸው ። ይኸንንም ስንል በሥጋ ግንኙነት የሚደረግ ፍቅር ማለታችን እንዳልሆነ ግልጥ ይሁን ። ዳሩ ግን ከጌታ የሚሰጥ ከላይ የሆነ ፍቅር ነው ። እንዲህ ያለው ፍቅር ነው እስከ መጨረሻ የሚዘልቀው ። ራስን ብቻ መውደድ ያልሆነ ፍቅር ፥ ከግል ጥቅም ይልቅ የሌላን አብልጦ የመመልከት ፍቅር ። ጥሩ ጋብቻን የሚፈጥር ፍቅር በአንድ ጊዜ ተቀነባብሮ የሚያልቅ አይደለም ። ለማደግና ለመጠናከር ረጅም ጊዜን ይጠይቃል ። እንግዲህ ከጋብቻ በፊት የቃል ኪዳን ጊዜ ያስፈለገበት አንደኛ ምክንያት ለዚህ ነው ። የቃል ኪዳኑ ጊዜ በሳምንትና በወር ብቻ የሚያበቃ ከሆነ ዓላማውን ለማከናወን በጣም አጭር ጊዜ ይሆናል ። ከጋብቻ በፊት ያለውን የመተዋወቅያና የቃል ኪዳን ጊዜ በጣም አጭር ማድረግ አስተዋይነት አይደለም ።

አንዳንድ ተጋቢዎች ደግሞ ከጋብቻቸው በፊት ትምህርታቸውን ጨርሰው ማጠናቀቅ እንዳለባቸው ያቅዳሉ ። ይሄም የጋብቻውን ጊዜ ለብዙ ዓመታት ያራዝመዋል ። ከዚህም በቀር ወንድየው እነርሱን የሚያረካ ወፍራም ደሞዝ የሚያስገኝለትን ሥራ እስኪያገኝ የሚጠብቁም አሉ ። አንዳንዴም በመካከሉ የቤተሰብ ሕመም የመሳሰሉ ነገሮች ጣልቃ ይገቡና ሰውዬውን ነፃ ስለማያደርጉት ጋብቻውን ያራዝሙታል ።

ብዙ የተፋጠነ ጋብቻ በጥበብ እንዳልሆነ ሁሉ በጣም የተንዛዛም የጋብቻ መራዘም በጥበብ የተወጠነ አይደለም ። እግዚአብሔር ተጋቢዎቹን አንዳቸውን ወደ ሌላቸው በመምራት ከፋቀራቸው ያለ አንዳች ምክንያት ለረጅም ጊዜ እንዲቀመጡ አይፈልግባቸውም ። የጋብቻው ጊዜ በጣም የተራዘመ እንደሆነ ብዙ ከመቀራረብ የተነሳ ከጋብቻቸው በፊት በሥጋ ግብር እርስ በርሳቸው ለመሰጣጣት ይፈተናሉ ። በወንድና በሴት መካከል ያለው የመፈቃቀድ ባሕርይ ከእግዚአብሔር የተሰጠ

ከማታውቀው ቤተሰብ መኖር እንደምትጀምር ሲሰማት ፍርሃት ፍርሃት ይላት ጀመር ። እርስዋም ፍርሃትዋን በሚስጢር ለጥላሁን ነገረችው ። መጋቢ ደስታ በዚህ ጉዳይ ላይ ደግሞ ሊመክሩዋቸው ፈቃደኛ እንደሚሆኑ ይገባቸዋል ።

ትምህርት ፦— እርሳቸውም በክፍሉ የሚገኙትን የትምህርቱን ተካፋዮች ፦— «ከጋብቻ የምትጠባበቁት ነገር ምንድር ነው ?» ብለው ጠየቁዋቸው ። «እንድ ሰው ጋብቻ የሚሰጠውን ማንኛውንም ነገር መቀበል የሚችለው እርሱ ለጋብቻ አቋም በሰጠው በር መጠን ነው ። እያንዳንዳቸው ተጋቢዎች በነፍስ ወከፍ ለጋብቻቸው የግል የሆነ ግብ ማበጀት አለባቸው ። በሕብረትም የእነዚህን ግቦች ውጤት ለማግኘት መሥራት አለባቸው ።» በዚህን ጊዜ የእያንዳንዳቸው ራስ በስምምነት ዝቅ አለ ። ሀሳቡ በእውነት የሚደገፍና ጥበብን ያዘለ ይመስላል ።

(ምናልባት ለጋብቻ ግቡ ምን እንደሆነ ያስረዱ እንደሆነ ያላቸውን አስተያየት እንዲሰጡ ምዕመኑን ጠይቅ ። እነርሱ የአንዳንድ ነገሮችን ስም ከጠቀሱልህ በኋላ ከእነርሱ የወሰድከውን ሀሳብ አስፋፋና የሚከተሉትን ነገሮች አክልበት ።)

አንድ አስፈላጊ የሆነ የጋብቻ ግብ ፍቅርና መተሳሰብ ያለበት ቤት ለማቋቋም ፤ እንደኛው በሌላው ላይ በሚደርስበት ነገር ተቆርቋሪነቱን ማወቅ ነው ። እያንዳንዳችን አንዳችን ለሌላችን ታላቅ ፍቅር በውስጥ ስላለን ይህን በውስጣችን የሚቃትተውን ፍቅር ሳንሰውር አንዳችን በሌላችን ያለንን ደስታ ከመናገር አለመቆጠብ ነው ። ከሌላ ሰው ይልቅ አንዳቸው ለሌላቸው የመጀመሪያውን ስፍራ እንደያዙ ማሳወቅ ደግሞ ይገባል ። በመጋቢ ደስታ ክፍል የነበሩ ምዕመን በሞላ ፍቅር ሊያድግና ሊዳብር እንደሚገባው ተስማሙ ። «የዳበረ ፍቅር ማለት ምንድር ነው ?» ብለው ጠየቁ ። (ይህን ጥያቄ ምዕመኑ ይመልሱ ።) የዳበረ ፍቅር ማለት ምንም ዓይ



ነት የመስዋዕትነትን ብድራት ሳይጠይቁ ራስን አሳልፎ ለሌላው መስጠት ነው ። ይኸውም ሌላውን በደስታ ማገልገል ማለት ነው ። የዳበረ ፍቅር ላደረገው ቸርነት ብድር ወይም ወረታ አይፈልግም ። ሌላውን በማበረታታት ይረዳል ። ስሕተትንም ያልፋል ፤ ያለፈውን ስሕተት ይረሳል ፤ ሊመጣ ያለውንም ተስፋ በደስታ ይተነብያል ።

ሌላው ደግሞ መግባባት ነው — በመሠረታዊ ነገር ላይ መስማማት ፤ ይኸም ማለት ተጋቢዎቹ ተመሳሳይ ፍላጎት ይኖራቸዋል ማለት ነው ። ይህ ዓይነቱ ነገር በተለይ ከቤተ ክርስቲያን ጋር ለሚያደርጉት ሕብረት የበለጠ አስፈላጊ ነው ። ተጋቢዎቹ የተለያየ ቤተ ክርስቲያን አባላት ከሆኑ ከጋብቻ በኋላ የማንኛው ቤተ ክርስቲያን አባላት መሆን አለባቸው ? (ምን መወሰን እንዳለባቸው እስቲ ምዕመኑ ሀሳብ ይስጡበት ።) ለቤታቸው ይበልጥ ቅርበት ወዳለው ቤተ ክርስቲያን ለመሄድ ይፈልጉ ፣ እንዲሁ ውሳኔውን እነርሱ ይጨርሱት ። ወይም ደግሞ የእነርሱ አገልግሎት ይበልጥ የሚፈለግበት ቤተ ክርስቲያን ካለ ደግሞ እዚያ ሄደው ቢያገለግሉና ቢያመልኩ መልካም ነው ። ጓደኞቻችን በሚሔዱበት ቦታ ስንሔድ ደስ የሚያሰኝ ቢሆንም እንኳ ይህ ለምንወስነው ውሳኔ አጥጋቢ ማረጋገጫ ሊሆነን አይገባም ። ይህ ጉዳይ ሳይጋቡ በፊት አስቀድመው ጸልየውበት ሊወስን የሚገባ ነገር ነው ። ምክንያቱም በብዙ ቤተሰብ ቅራኔንና ጥልን የፈጠረ በመሆኑ ነው ።

ሌላው የመግባቢያና የመተሳሰቢያው መንገድ ደግሞ ሊኖራቸው ስለሚገቡ ልጆች ቁጥር በሕብረት መወሰን ነው ። ምንም እንኳ ሊኖሩዋቸው የሚገባቸውን የልጆች ቁጥር ለመመጠን ባይችሉም ለጠባብና ለሰፊ ቤተሰብ ቁጥር መወሰን ያስፈጋቸዋል ። ልጆቻቸውን በምን ዓይነት ቁጥጥር ማሳደግ እንዳለባቸውም መወያየት አለባቸው ። ሁለቱም ተመሳሳይ ወይም እኩል የሆነ ቁጥጥር ያደርጉ እንደሆን በጣም እርግጠኛ መሆን አለባቸው ።



እሙኛማዎቹ ወደመጋቢ ደስታ ቤት ጠቃሚ ምክር ለማግኘት ሲሄዱ



እነርሱም እንዳቸው ለሌላቸው ተደጋጋፊዎችና ታማኞች በመሆን እንዲጠብቃቸው ወደ ጌታ ጸለዩ ።

ጸሎት ፦ ፍቅር በቤታችሁ ውስጥ በመካከላችሁ እየተገለጸ ነው ?

በሁሉም ነገር ለባሎቻችሁና ለሚስቶቻችሁ ታማኞች ናችሁ ?

ዘወትር በሥራህ በመግለጥ አፍቃሪና ታማኝ እንድትሆኑ እግዚአብሔር እንዲረዳችሁ ጠይቁት ።

ክፍል ፫ — ትምህርት ፰

# ክርስቶስን የሚያከብር ቤትና ዋስትና

የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ፦ መዝሙር ፻፩ (፻) ፣ ፩ — ፰

የቃል ጥናት ፦ ኢያሱ ፴፪ ፣ ፲፰

ዓላማ —.በቤታችን ጌታን ለማስከበር መጓጓትና ዋስትና ያለው ጋብቻ እንዲኖረን

መግቢያ ፦ ጥላሁን ፦ «ለቤታችን ለሚያስፈልጉን ሌላ ተጨማሪ ነገሮች አሉን» ሲል ንግግሩን ቀጠለ ። «ክርስቶስ የሚከበርበት ቤት እንዲኖረን እንፈልጋለን» አለ ። «ዋስትና እንፈልጋለን ፣ ጋብቻችንም ሕብረት ያለው አንድ የቤተሰብ አካል እንዲሆን እንሻለን» ብሎአል ።

ከቀድሞው ትምህርታችን ወዲህ ምንና ምን ግቦችን አሰባችሁ ? (እነርሱ በሚሰጡት ሀሳብ ላይ ተወያዩበት ።) አቶ ኃይሌ እንደኛው ግብ ለጋራ ጥቅም የሚደረግ አንድነትና ሕብረት ነው ብለዋል ። ሌላው ደግሞ መንፈሳዊ እድገት ነው አሉ ። መጋቢው ደግሞ በዚህ ትምህርትና በሚከተለው ትምህርት ላይ የበለጠ ማብራርያ እንሰጥበታለን አሉ ።

ትምህርት ፡— «እኔና ቤቴ ግን እግዚአብሔርን እናመልክለን ።» ይህ በኢያሱ ፳፬ ፣ ፲፭ ላይ የተጠቀሰው ሀሳብ የእያንዳንዳቸው ተጋቢዎች ሀሳብ መሆን አለበት ። ይሄም ማለት ከማንኛውም ሰው ጋር በሚያደርጉት ተባብር ሁሉ ጌታን ያስከብራሉ ማለት ነው ። ከዚህም የተነሳ ለቤታቸው ፣ ለጎረቤቶቻቸው ፣ ለጓደኞቻቸውና ለቤተሰባቸው ምሳሌ ይሆናሉ ። ቤታቸውም እነርሱ በሕብረት ሆነው የእግዚአብሔርን ቃል የሚያነቡበትና አብረው የሚጸልዩበት ሥፍራ ይሆናል ። በሚከተለው ትምህርታችን ስለ ክርስቲያን ቤተሰብ የበለጠ እንማራለን ። አሁን ግን የእያንዳንዱ የክርስቲያን ቤት ጌታ የሚከበርበት መሆን እንዳለበት እንወያያለን ።

ዋስትና ያለው ኑሮ ሁለቱም ተጋቢዎች የሚፈልጉትና ሊኖራቸውም የሚገባ ነገር ነው ። ይሄም ማለት ለሴትዮዋ ሥጋዊ ጥበቃ እንዲወሰድላትና የመኖርያ ቤት እንዳላት ማወቅዋ ነው ። እንደዚሁም የሚያስፈልጓቸውን ነገሮች ለመግዛት በቂ ገንዘብ እንዳላቸው ማወቅዋ ነው ። በልየው ደግሞ ሚስቱ እንደምትወደውና ከእርሱ ጋር የተጣበቀች መሆንዋን ሲያውቅ ይህ ለእርሱ የተጨበጠ ዋስትናው ነው ። ሁለቱም አንዳቸው ለሌላቸው ስላላቸው ፍቅር ዋስትና ሊኖራቸው ይፈልጋሉ ። ይሄም ማለት ባልየው ብዙ ጊዜ ሚስቱን እንደሚወዳት ሊያረጋግጥላት ይገባል ። ሚስትየዋም በቃልዋ እንደምትወደው ትናገር ። ምግቡን ስታዘጋጅለትና ለቤቱ ጥንቃቄ ስትወስድ እንደምትወደው መግለጥዋ ነው ። ያም ሆኖ ሁለቱም መዋደዳቸውን በቃል መግለጥ አለባቸው ። በዚህም አንዳቸው ለሌላቸው ባላቸው ፍቅር ዋስትና ይኖራቸዋል ። በሕይወታቸውም የሚገጥማቸውን ችግር በአንድነት ለመቋቋም ይጠናከራሉ ።

ለተጋቢዎቹ ግዴታ አስፈላጊ የሆነ በቂ የዋስትና ገንዘብ ሊኖራቸው ይገባል ። ተቀማጭ ገንዘብ የቤትና የጋብቻ አስፈላጊ ክፍል ነው ። «ለአንድ ሰው በቂ የሆነ ነገር ለሁለት ሰዎች ይበቃል» የሚለው የዱሮ ተረት



እውነት አይደለም ። አንድ ሰው ሳያገባ በፊት ለመተዳደርያው የራሱ ደሞዝ የማይበቃው ከሆነ ገንዘቡን የሚያወጣበት መንገድ ካልተሻሻለና ልዩ ተጨማሪ ገንዝብ ማግኛ በር ካልኖረው በቀር በቀድሞው ሁናቴ ሚስት ቢያገባ ጨርሶ ሊረዳት አይችልም ።

ተጋቢዎቹ ለቤታቸው የሚያስፈልጋቸውን ያህል አስቀድመው መተመን ይኖርባቸዋል ። የሰው ቤት አስፈላጊ የሆነው መጠን ምን ያህል ነው ? (ለቤት አስፈላጊ የሆኑትን ነገሮች ምዕመኑ ራሳቸው በዝርዝር ይናገሩ ።) አዎ ፣ ለቤተሰብ ምግብ ፣ ልብስ ፣ አስራትና ምጽዋት ፣ ድንገተኛ ለሚደርሱ አደጋዎች ፡— ማለት በፕላን ውስጥ ያልገቡ ወጭዎች ድንገተኛ ሕመምና ሊታለፉ የማይቻሉ አጋጣሚዎች (የተሰበረ ምጣድና ሌላ የሚያስፈልግ እቃ) በተለይ ሕፃን በሚወለድበት ጊዜ ብዙ ገንዘብ ያስፈልጋል ።

ገንዘብ የምታወጡባቸውን ነገሮች ከጻፋችሁ በኋላ በግምት ለእያንዳንዳቸው ምን ያህል እንደሚያስወጣችሁ በጽሑፍ አስፍሩት ። እናንተ ከምታገኙት በላይ እንዳይልቅ ተጠንቀቁ ። የክርስቲያን ገንዘብ የእግዚአብሔር ስለሆነ እግዚአብሔር የሰጠውን በምስጋና መቀበል አለበት ። እግዚአብሔር በጊዜው በመጠቀም እንዲመራው ጸሎትን በተሞላ ሁናቴ መጠየቅ አለበት ። እያንዳንዱ ተጋቢ ምን ያህል ገንዘብ እንዳላቸው ከወቀ በኋላ ባላቸው ለመኖር የበለጠ ፈቃደኛ ይሆናል ።

ገንዘብ ሲያስፈልገንና የሚያስፈልገን ደግሞ ከምንቀበለው ገንዘብ በላይ ከሆነ ምን ማድረግ አለብን ? (ምዕመኑ በዚህ ነገር ላይ ሀሳብ እንዲሰጡበት ይደረግ ። ያለ ምንም ጥርጣሬ ጥቂቶቹ ሚስትዮዋ ሥራ መያዝ አለባት የሚሉ ይሆናሉ ።) ሚስትዮዋ ከቤትዋ ውጭ ሥራ ቢኖራት መልካም ይሆናልን ? እንደማንኛቸውም የቤት ጉዳይ እንደሚያስነሳቸው ሌሎች ብዙ ጥያቄዎች ሁሉ ይሄም ጉዳዩ በሚመለከታቸው ግላዊ ቤተሰቦች እንደገባናቸው ለራሳቸው በራሳቸው የሚመለስ ነው ። ምናል

ባት አንዳንድ የኑሮ ቀዳዳዎችን ለመድፈን ሲባል ሚስቶች ሠራተኞች ሊሆኑ ይገባ ይሆናል ። ምናልባት እርስዋ ሥራ የሥትፈልገው ቅንጦትን ለማትረፍ ስትል ብቻ ከሆነ ከቤት ውጭ የምታሳልፈው ጊዜ ጠቃሚ አይሆንም ። በኋላ ልጆች በምትወልድበት ጊዜ ደግሞ በየጊዜው ልጆችዋ የእርስዋን በቤት መገኘት ስለሚፈልጉ እናትየዋ ልትገኝበት የሚገባ የተመረጠውና ዋነኛው ስፍራ ቤትዋ ነው ። ያም ሆኖ በቤት ያለመገኘትዋም ነበር በዚሁ መጠን አስፈላጊ የሚሆንበት ጊዜ አለ ። ተጋቢዎቹም በቤት የሚፈለጉበትን ጊዜ ለሟሟላት እንዲችሉ በክርስቶስ መታመን ይኖርባቸዋል ። በመሠረቱ የሚስት ትክክለኛ ሥፍራ በቤት መሆን ነው ። ነገር ግን በቤተሰብ ላይ የኑሮ ክብደት ከመጣና የማይወጡት ከሆነ በሥራ መስክ ላይ ብትሰማራና ለቤታቸው መቋቋሚያ የሚሆኑትን ነገሮች ብታስገኝ ግዴታ ነው ። በጊዜው ይኸንን ተጨማሪ ኃላፊነት እንድትሸከም ጌታ ጸጋውን ያበዛላታል ።

<u>ትምህርቱን በሥራ ላይ ማዋል</u> ፡—

በመጨረሻም መጋቢ ደስታ መልሱን በጸሎት መንፈስ ሆነው በግል ለጌታ እንዲመልሱ በትምህርቱ ፍጻሜ ላይ ይህን ጥያቄ ጠየቁዋቸው ፡— «እነዚህ ግቦች በየቤታችሁ የተፈጸሙ ናቸውን ? በሥራህና በሥራሽ ሁሉ ክርስቶስን የሚያስከብር ተግባር እየፈጸማችሁ ነውን ? ባሎች ፣ ሚስቶቻችሁ በእናንተ ፍቅር ዋስትና አላቸው ? የገቢያችሁን ሁሉ ምንጭ ሳትሰውሩ ግልጥ አድርጋችሁ ከሚስቶቻችሁ ጋር ትነጋገሩበታላችሁ ? ሚስቶች ፣ ባሎቻችሁ በእናንተ ፍቅር ዋስትና አላቸው ? ልጆችስ በእንቺ ፍቅር ዋስትና እንዳይኖራቸው ያለ ምክንያት በዘፈቀደ በግዴለሽነት የትም ጊዜሽን ታሳልፊያለሽ ?

<u>ጸሎት</u> ፡— ይህን ጥያቄ ስንመልስ እውነቱን እንድንነግረው ታማኞች እንድንሆን እንዲረዳን እንጠይቀው ።



ምናልባት በአንዳንድ ነጥቦች ላይ ታማኝነታችሁን አፍርሳችሁ እንደሆነ መልሳችሁ ለማረም እርዳታውን እንዲሰጣችሁ ጠይቁት ።

ክፍል ፫ — ትምህርት ፱

# መንፈሳዊ እድገት ፣ አባሪነትና ሽርክነት

<u>የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል</u> ፡— የሐዋርያት ሥራ ፲፰፥ ፩—፫ ና ፲፰—፳፩ ና ፳፬—፳፮

<u>የቃል ጥናት</u> ፡— ሮሜ ፲፮፥፫

<u>ዓላማ</u> —.እያንዳንዱ ተጋቢ የጋብቻ ኃላፊነት እንደሆነ አውቆ መቀበል ፣
.ኃላፊነት በሙሉ ሰውነት ደረጃ እንዲቀበሉ

<u>መግቢያ</u> ፡— ጽጌ አብዛኛውን ጊዜዋን የምታሳልፈው እናትዋን በመርዳትና ብዙ ለባለትዳሮች የሚያስፈልጉ ልዩ ልዩ ሞያዎችን በመማር ነው ። ለቤትዋ እቅድ በምታወጣበት ጊዜ በጣም ደስ እያላት ነበር ። አንድ ቀን ግን የሕይወት ጥላ የሆነ ደመና ዘረባት ። ይኸውም የወንድምዋ መታመም ነበር ። እናትዋ ለወንድምዋ የምታደርግለትን እንክብካቤና የፊትዋን ኀዘን እየተመለከተች ሳለ እናትዋ ወንድምዋን በማስታመም ምክንያት ልትሠራው ያልቻለችውን የቤት ሥራ ታጠናቅቅ ጀመር ። እርስዋም በሥራ ላይ እያለች አንድ ሀሳብ ወደ አእምሮዋ መጣ ። እርስዋም ፡— «ይኸም እኮ የጋብቻ ሌላኛው ክፍል ነው» በማለት አሰበች ። እኔ ያሰብኩት ከምወደው ጋር ስለማቋቁመው ደስተኛ ቤት ብቻ ነበር ። ለካ በእኔም ቤት እንዲህ ያለው ጊዜ ሊመጣ ይችላል ። ለመሆኑ እንደ እናቴ ይኸንን ኃላፊነት የመሸከም ችሎቻ ይኖረኝ ይሆን ?»

<u>ትምህርት</u> ፡— መንፈሳዊ እድገት ማለት ምን ማለት ነው ? መንፈሳዊ እድገታችንንስ እንዴት አውቀን

መናገር እንችላለን ? (እስቲ በዚህ ላይ ምዕመኑ ያላቸውን
አስተያየት ይስጡበት ።) ወደ ቤታቸው በሚመጣው
ችግር ውስጥ መንፈሳዊ እድገትን እንዲያገኙ የእያንዳ
ንዱ ተጋቢዎች ምኞት መሆን አለበት ። ምክንያቱም
በዚህ ውስጥ የእግዚአብሔርን እርዳታ በመጠየቅ በጥ
በብ የተወሰነ ውሳኔን ለመውሰድ ስለሚረዳቸው ነው ።
ለእግዚአብሔር ማድረግ ያለበትን ነገር ሊነግሩት አይገ
ባም ። በዚህ ፋንታ ግን ምን ማድረግ እንደሚኖርባቸው
መጠየቅ ይገባቸዋል ። ሊያደርጉት ያለውንም እርምጃ
አእምሮአቸውን መጠየቅ የለባቸውም ። በዚህ ፋንታ
ግን እርምጃው ምን እንደሆነ እስኪያሳያቸው ድረስ ጠይ
ቀው የጥያቄአቸውን መልስ እስከሚያገኙ መታገስ አለባ
ቸው ። ችግርና መከራን የመቀበል ሁኔታ መንፈሳዊ
እድገትን ይለክል ። መንፈሳዊ እድገት ያላቸው
ከሆነ ስለሚያደርጉት ነገር እርግጠኞች ናቸው ።
በሚከፋቸውም ጊዜ እግዚአብሔርን ማመስገን ይማ
ራሉ ። ይሄንን በመገንዘብ በዚህ ችግር ውስጥ ሊማሩት
የሚገባ ለእነርሱ የሚሆን አንድ ትምህርት አለው ።

አብሮ የመኖር ሕብረት ደግሞ ሌላኛው የጋብቻ
ግብ ነው ። እግዚአብሔር ሰውዬው ብቸኛ መሆኑን
ስላወቀ ሴትን ፈጠረለት ። «እግዚአብሔርም ያደረገውን
ሁሉ አየ ፤ እነሆም እጅግ መልካም ነበር ፤» (ዘፍጥረት
፩ ፥ ፴፩) የፈጠረው ፍጥረት ሁሉ መልካም ነበረ ። ይኸ
ውም ሊደሰቱበት የሚገባ ነገር ነው ። ባልና ሚስቶችም
አንዳቸው በሌላቸው ደስ ሊሰኙ ይገባል ። በሚያስደስ
ትም ነገር ሆነ ቁም ነገር በሆነ ነገር ሁሉ ሊወያዩና ሊጨ
ዋወቱ ይገባል ። ከሌሎችም ጋር ወዳጅነትንና ሕብረትን
መመስረት አለባቸው ። ከመጋባታቸው በፊት አብረው
ሲሆኑ ሁለቱም ብቸኝነትና ባዶነት ከተሰማቸው ከተጋ
ቡም በኋላ ነገሩ ስለማይሻሻል ባይጋቡ ይሻላቸዋል ።

መጋቢ ደስታ በመጨረሻ ላይ ማብራርያ የሰጡት
ነገር ባልና ሚስቶች አንዳቸው ለሌላቸው የአንድ አካል



ክፍል ተባባሪ ናቸው ። ከዚህም በቀር እያንዳንዳቸው
በነፍስ ወከፍ ከእግዚአብሔር ጋር ሕረብት አላቸው ።

መጽሐፍ ቅዱስ ወንድ የሴት ራስ ነው ይል የለ
ምን ? የመጽሐፍ ቅዱስን ትምህርት ከተከታተልን ተባ
ባሪ ሊሆኑ ይገባቸዋል ? (ምዕመኑ ይወያዩበት ።) ይህ
ማለት ባል የቤት ራስ አይደለም ማለት አይደለም ፤ ነገር
ግን በመሪነቱና በባለስልጣንነት በታው ሚስቱን ገለል
ተኛ ሳያደርግ በሚያስፈልገው ነገር ሁሉ ይተባበራታል ።
እርሱም በቀጥታ አሳሳቢ በሆኑበት ነገሮች ሁሉ ተሳትፎ
እንዳላት በማወቅ መተባበር የምትችል የጠራ አስተሳሰብ
ያላት የእግዚአብሔር ፍጡር መሆኑዋን መዘንጋት የለበ
ትም ። እርሱ አውራ ለሆኑት ነገሮች ውሳኔ ያስተላል
ፋል ። እንደተባባሪነትዋ ደግሞ የእርስዋን ፍላጎትና
አስተሳሰብ ይቀበላል ። በአንድነት እያንዳንዳቸው የሆኑ
ትን ነገር በተለያዩም ጊዜ እንደዚያው ይሆናሉ ።

በሐዋርያት ሥራ ፲፰ ላይ አቂላ ስለተባለ ሰውና
ሚስቱ ስለሆነችው ስለጵሪስቂላ የተነገረ ታሪክ እናገኛ
ለን ። እነዚህ ሰዎች ባደረጉት ተባብሮና አንድነት እንደ
ምሳሌ ለመጥቀስ መልካም አርአያ ሆነው ቆመዋል ።
እነርሱም በአንድነት ድንኳን እየሠፉ በአንድነት ደግሞ
ጌታን ያገለግሉ ነበር ።

አንደኛው ሽርክነት ደግሞ አጥጋቢ ውጤት እንዲ
ያገኝ የሕብረትን ቡድን ማጠናከር ነው ። እያንዳንዱ
ተባባሪ የራሱን የቡድን ክፍል በመርዳት የግሉን ድርሻ
ይሠራል ። ጳውሎስ ስለ ቡድኑ ውጤት ሲናገር ፦
«በአንድ ሀሳብ ተስማሙ ፤ አንድን ነገር በአንድ ዓይነት
ሀሳብ መመልከት ።» (ፊልጵስዩስ ፪ ፥ ፪ ፤ ፩ኛ ቆሮንቶስ
፩ ፥ ፲ ።) የሥራ ባልደረቦቹ በአንድ ነገር ላይ ስላላ
ቸው አስተያየት በግልጥ የሚወያዩ ከሆነ አንዱ በአንዱ
ነገር ላይ ያለውን አስተሳሰብና ውሳኔ ሳይነገረው አስቀ
ድሞ ሊረዳ ይችላል ። የቡድኑ አባሎች አንዳቸው ለሌ
ላቸው ታማኞች ናቸው ። በሕብረት በደነገጉት ሕግ ላይ
አያላግጡም ። አንዳቸውም በሌላኛው ላይ አይመቀ
ኙም ። በሕብረት አጥቂያቸውን ለማሸነፍ ይተባበራሉ ።

በቅርብ ጊዜ አዲስ የተመሰረተውን ቤት ጨምሮ በጠቅላላው ሦስት ቤተሰቦች ተባብሮ ያደርጋሉ ። እነዚህም የሙሽራው የወላጆች ቤት ፣ የሙሽራይቱ የወላጆች ቤትና ያዲሶቹ ተጋቢዎች ቤት አንድነት ይመሠረታል ። ያም ሆኖ ከጋብቻቸው በፊት በቅርብ ቢተዋወቁ በጣም መልካም ነው ። የቀሩት ቤተሰቦች ሁሉ እነዚህን አዲስ ቤተሰቦች በወቁዋቸው ጊዜ አካባቢው ተለውጦ እነዚህ ቤተሰቦች የሚያድጉበትና የሚጠናከሩበት በር ይከፈታል ። ሁለቱም አዲስ ቤተሰቦች አንድ የሆነ የተቀራረበ ቤተሰብ ሲመሠርቱ ቀድሞ ጥለው የመጡአቸውን ቤተሰቦች ከቅርበት ሕብረታቸው ይገልሉአቸዋል ። እርግዋ አንዳንድ ምክር ቢያስፈልግ ይጠይቁአቸዋል ። ነገር ግን በአዲሱ ቤተሰብ ላይ የሚመጣውን ችግር የሚወጡት ራሳቸው ናቸው ።

<u>ትምህርቱን በሥራ ላይ ማዋል</u> ፣—

ጥላሁንና ጽጌ ለጋብቻ የሚያዘጋጁአቸውን አንዳንድ ግቦች ቀደም ብለው ተወጥተዋቸዋል ። አንዳንዶች ሕብረታቸውን ለማዳበር ጊዜ ይወስድባቸዋል ። ጥቂቶቹ ደግሞ ብዙ ጸሎትና ውይይት ያስፈልጋቸዋል ።

ባለፉት ሦስት ተከታታይ ትምህርቶች እንደተወያየነው መሠረት ጋብቻችሁ በምን ሁናቴ ላይ ይገኛል ? እነዚህን ግቦች ለመድረስስ ምን እያደረጋችሁ ነው ?

ጥላሁንና ጽጌ ወደ ጋብቻቸው ሊመጡ ያሉትን ችግሮች መቋቋም እንዳለባቸው ተገነዘቡ ። ምናልባት ሕመም በቤተሰባቸው ቢመጣ ፣ እግዚአብሔር ወደ ሕይወታቸው የሚልከውን ፈተና በትዕግሥት መቀበል የሚችሉ እንደሆነና በመንፈሳዊ ሕይወታቸው አድገው እንደሆን ያውቃሉ ።

<u>ጸሎት</u> ፣— በሕብረት ሆናችሁ ጌታን ማገልገል እንድትችሉ የኑሮ ጓደኞችሁ ከእናንተ ጋር የተጣመረ ትብብር እንዲሆንና እንድትሆን እግዚአብሔር እንዲረዳችሁ ጸልዩ ። በመንፈስም ከክርስቶስ ጋር ሕብረት ስላላ





ወ/ት ጽጌና አቶ ጥላሁን በሠርጋቸው ዕለት

ችሁ በመንፈሳዊ ሕይወታችሁ እንድታድጉና እንድትጎለ ምሱ እንዲያደርጋችሁ በጸሎት ጠይቁት ።

| |
|---|
| ክፍል ፬ |
| ትምህርት ፲ — ፲፬ |
| በጋብቻ ያለ የልብ መቀራረብ ወይም ሚስጢረኛነት |

የክፍሉ ዓላማ ፦ ጋብቻ ባልና ሚስትን በሥጋዊ ሆነ በመንፈስ እንደሚያጣምራቸውና አንድ አካል እንደሚያደርጋቸው ለማመልከት ነው ።

የክፍሉ ጥቅስ ፦ ማርቆስ ፲ ፥ ፰

## ክፍል ፬ — ትምህርት ፲

# ሚስጢራዊ ሕብረት

የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ፦ መኃሊ ፪ ፥ ፩ — ፯

የቃል ጥናት ፦ ዕብራውያን ፲፫ ፥ ፬

ዓላማ — .የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት እግዚአብሔር የጋብቻ እቅድ ማሳየት፣

.ባሎችና ሚስቶች የበለጠ አንዳቸው በሌላቸው ደስ እንዲሰኙ፣

.ያላገቡ ወጣቶች የተለየና የተቀደሰ ክፍል ለማስተማር

መግቢያ ፦ ጥላሁንና ጽጌ ብዙ ጊዜ አብረው ከመሆናቸው የተነሳ በግብረ ሥጋ ፈቃድ የመፈላለጋቸው ሁናቴ በጣም እየተጠናከረ ሄደ ። እነርሱም የጋብቻቸውንና የወደፊት የቤተሰባቸውን ግብ በነፃነት ይወያዩ ጀመር ። ነገር ግን ግብረ ሥጋን ስለሚመለከት ነገር ከመወያየት እየተጠነቀቁ ነበር ። ከዚህ በኋላ ግን አንድ ምሽት መጋቢ ደስታ ወደዚህ ትምህርት ደርሰው ሲያስተምሩ በመጀመሪያ ከደነገጡ በኋላ መሽኮርመምና ማፈር ጀመሩ ። ቢሆንም ትንሽ እንደቆዩ ነገሩ ቁም ነገርን ያዘለ እንደሆነ ሲረዱ ይህም ከእግዚአብሔር እቅድ አንዱ መሆኑን ተገነዘቡ ።



ትምህርት ፦ የሚጋቡ ሰዎች ከመጋባታቸው በፊት ትክክለኛ የሆነ የግብረ ሥጋ እውቀት ሊኖራቸው ይገባል ። እነርሱም አንዳቸው በሌላቸው ደስ ይሰኙ ዘንድ መፍጠሩን በመረዳት እግዚአብሔር በጋብቻቸው በዚህም እንዲጠቀሙ አቅዶአል ። በመካከላቸውም የሚፈጸመው የግብረ ሥጋ ፈቃድ የእግዚአብሔር በረከት አለበት ። ይኸንን ነገር አሳፋሪና እርካሽ እንደ ሆነ አድርጎ ያስገመተው ሰው በገዛ አሳቡ በኃጢአት ምክንያት በመጣው መዘዝ ነው ። ከዚህም ውጤት የተነሳ ብዙዎቹ ሰዎች አሳፋሪና አጸያፊ ነገር አድርገው ሊገምቱት ችለዋል ። በዚህም ምክንያት ይህ አርዕስት በውይይት እንዳይነገር እንደ አጸያፊ ተቆጥሮ ተገልሎአል ።

ምሳሌ ፭ ፥ ፲፰ እናንብብ ። ባል ፦ «ከጉብዝናህ ሚስት ጋር ደስ ይበልህ» ተብለሃል ። ባልና ሚስት መፈጠራቸው አንዳቸው በሌላቸው እንዲደሰቱ ነው ። ግብረ ሥጋ ግንኙነት አንደኛው የሚደሰቱበት መንገድ ነው ። እግዚአብሔርም አዳምና ሄዋንን ፦ «ብዙ ተባዙ ምድርንም ሙሉአት» ብሎአቸዋል ። (ዘፍጥረት ፩ ፥ ፳፰ ።) ልጆች ከፍቅር ጋብቻ በኋላ በውጤቱ እንዲወለዱ እግዚአብሔር የወሰናቸው ፍጥረቶቹ ናቸው ። እግዚአብሔር የፈቀደው የግብረ ሥጋ ፈቃድ በዚህ ምድር የሚገኙት ፍጡራን ሁሉ የተፈጠሩበት መንገድ ነው ። ተጋቢዎቹ በልጆቻቸው በኩል የሚመጣው ኃላፊነት የማይቀበሉ ከሆነ በግብረ ሥጋ በኩል ለሚያደርጉት ግንኙነት ብስለት ስለሌላቸው ለጋብቻ ብቁአን አይደሉም ። ስለዚህ ጋብቻቸው ጥቂት ቢዘገይ መልካም ነው ። እርግጥ በሥጋቸው ያደጉ ሊሆኑ ይችላሉ ። ሆኖም ፍቅራቸው ግን ራስ ወዳድነት አለበት ። ለጓደኛቸው ግድ ሳይኖራቸው የራሳቸውን እርካታ ብቻ ይፈልጋሉ ። ብስለት ያለው መንፈሳዊ ፍቅር ሌላው ደስ እንዲለው ለመስጠት ፈቃደኛ ነው ።

የባልየው የበላይነትና የቤተሰቡ አውራነት በዚህ በጋራ አጠቃላይ የቤተሰብ እለታዊ የኑሮ አመራር ውስጥ

ይታያል ። እርሱም ለባለቤቱ በሚያሳያት እንክብካቤ የፍቅሩን መልስ እንድትሰጠው ያደርጋታል ። ከዚህም በቀር እርስዋ ደግሞ የእርሱ ቢጤ ሰው እንደሆነች መዘንጋት የለበትም ። የእርሱም ስሜት ለማርካት ብቻ የተሰጠችው እቃ አይደለችም ። እርሱ የሚገባትን ፍቅር ሲያሳያት የምትሰጠው መልስ ሁለቱንም የሚያረካ ይሆናል ። እንዳቸው የሌላቸውን ምቾት በመጠበቅ ወደ አንድ የጋራ ስምምነት መድረስ አለባቸው ። አንዳቸው የሌላቸውን ምቾት በመጠበቅ የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት ቢፈጽሙ ይህ ለእነርሱ በቅድስና የተለየ የፍቅራቸው ማዳበሪያ ነው ። እንዳቸው የሌላቸውን ምቾት የማይጠብቁ ከሆነ ደግሞ መበሳጨትንና መወራጨትን ያስከትላል ። ይሄም ቁም ነገር የሆነ የጋብቻ ክፍል ነው ። ቢሆንም አስፈላጊነቱ ተጋኖ መነገር የለበትም ። ሌሎቹ የጋብቻ ክፍሎችም የሚሰጡት ጥቅም እኩል ነው ። እነርሱም ከሆኑት በላይ ተጋነው ቢነገሩ ሕብረታቸውና አንድነታቸው ሐሰትና ጥቅመ ቢስ ይሆናል ።

ወጣቶች ወደዚህኛው የጋብቻ ክፍል በፍርሃት መምጣት የለባቸውም ። ማንኛውም አዲስ ግንኙነት አዲስ የሆነ መቀነባበርን ይጠይቃል ። በግብረ ሥጋ በኩል ያለው መቀነባበር አብዛኛውን ጊዜ በጣም ጥቂት ነው ። ይኸውም ሁለቱም አንዳቸው ለሌላቸው ፍቅር ሲኖራቸውና ሲተሳሰቡ ነው ።

በጣም የሚያሳዝነው ነገር አንዳንድ እጮኛሞችና ሌሎችም ወጣት የጋብቻቸው ቀን እስኪደርስ ድረስ ሳይታገሱ የግብረ ሥጋ ግንኙነትን አስቀድመው መፈጸማቸው ነው ። እርስ በርሳችን ስለተፋቀርን ነው የሚል ምክንያት ምንም ያህል የበዛ ቢሆን ነገሩ አስነዋሪ እንደ ሆነ ይቀራል ። ለመጋባት እቅድ አድርገናል ፣ ነገሩን አስተካክለዋለሁ ። እንደዚህ ያለው እርምጃ በክርስትና ሕይወት የሚገኘውን ፍቅር ጨርሶ የካደ ነው ። ከጋብቻ በፊት የሚደረግ ሩካቤ ሥጋ ፍጹም አይን ያወጣ ቁልጭ ያለ ስግብግብነት ነው ። ይሄም የሚደረገው የግልን



ስሜት ለማርካት ብቻ የሚደረግ እርምጃ ነው ። ይሄም አድራጎት ኃጢአት ነው ። (፩ኛ ቆሮንቶስ ፮፥፲፰)

<u>ትምህርቱን በሥራ ላይ ማዋል</u> ፦

መጋቢ ደስታ በትምህርቱ መጨረሻ ላይ ይህንን ጥያቄ ጠየቁ ። «ለሩካቤ ሥጋ ያላችሁ ዝንባሌ በጣም ደስ የሚል እግዚአብሔር ከቀድሞ ያቀደላችሁ ነገር ነው ? እንደ ባልና ሚስት ሆናችሁ ስትኖሩ ይህ ነገር ፍቅራችሁን የበለጠ እያዳበረላችሁ ነው ? ያላገባችሁትስ በዚህ ነገር ላይ ሀሳባችሁ ንጹህና ትክክል ነው ?»

ይህ ርዕስ ሩካቤ ሥጋ ሊንቁትና ሊያስወግዱት የሚገባ ርካሽ ነገር እንዳልሆነ አስገነዘባቸው ። ከዚህም በቀር የሩካቤ ሥጋ ውይይት በየትም ከማንም ጋር በአደባባይ የሚወራ ነገር አይደለም ። ለሩካቤ ሥጋ ግንኙነት ሥፍራ አለው ። ስለዚህ ለተገቢው ሥፍራ መጠበቅ ያስፈልጋል ።

ጥላሁንና ጽጌ አንዳቸው ለሌላቸው ያላቸው ፍቅር እያደገ ሳለና የመፈላለግ ስሜታቸውም ሲጨምር ኃጢአት እንዳያደርጉ እንዲጠብቃቸው ጸለዩ ። የጋብቻቸውም ጊዜ እየተቃረበ መጣ ። ለጋብቻቸው ቀን ለይተው በቅድስና የጠበቁትን ግንኙነት በኃጢአት ሊያበክሉት አልፈቀዱም ።

<u>ጸሎት</u> ፦ እግዚአብሔር በሩካቤ ሥጋ በኩል ያላችሁን አስተያየት ንጹህ እንዲያደርግላችሁ ጠይቁት ። ሀሳባችሁንና እርምጃችሁን እግዚአብሔር ንጹህና የተገታ እንዲያደርግላችሁ ጠይቁት ።

ክፍል ፬ — ትምህርት ፲፩

# በጋብቻ የሚገኝ ደስታ

<u>የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል</u> ፡— ምሳሌ ፴፩ ፥ ፲ — ፴፩

<u>የቃል ጥናት</u> ፡— ገላትያ ፭ ፡ ፳፪ — ፳፫

<u>ዓላማ</u> — · ደስታ የሚገኘው ደስታ በመሥራት ለማስረዳት ፤
· ደስታ የሚያስገኝ « ትንሽ ነገር » እንዳያደርጉ ለመምራት

<u>መግቢያ</u> ፡— አንድ ቀን ምሽት ጽጌ ቤተሰቡ ሁሉ ተኝቶ ሳለ በውድቀት ጨለማ አንድ ሰው መዝጊያቸውን ሲያንኳኳና አበትዋን ሲጠራ ሰማች ። «ምንድር ነው እሱ ?» ብላ አሰበች ። በማግስቱ ግን ታሪኩን ሰማች ። አንድ ጎረቤታቸው የሆነ ሰው ሥራ ቦታ አምሽቶ ሲገባ ልጆቹ እያለቀሱ ጠበቁት ። ባለቤቱም ጊዜው በጣም መፋጠኑን ዘንግታ አንድ ዘመድ የሆኑ ቤተሰቦች ልጅ ታሞ ስለነበር እነርሱን ለመርዳት ሄዳ ስትመለስ ብዙ አርፍዳ ገባች ። እራታቸው ስላልተዘጋጀ እያንዳንዱ ድምጹን ጎላ አድርጎ ይነጫነጫል ። አንዱ ሌላው የሚለውን በጽሞና ለመስማት ፈቃደኛ አልነበረም ። ስለዚህ ሁሉም ተናደው ስለነበር አንደኛው በሌላኛው ላይ ይጮሃል ። ክርክሩም ከማታ ጀምሮ እስከ ምሽት ድረስ እየጠፈ ሄደ ። በመጨረሻም የጎረቤት ሰው መጥቶ ጸጥታውን እስኪያስከብር ድረስ ታላቅ ጫጫታና ጩኸት ይሰማ ነበር ።

<u>ትምህርት</u> ፡— ጋብቻን ደስተኛ የሚያደርገው ምንድር ነው ? ገንዘብ ነውን ? ጥሩ ጥሩ እቃዎች ናቸውን ? ትልቅ ቤት ነውን ? (ተወያዩበት ።) ፍቅር ተጋቢዎቹን ወደ አንድ ቤተሰብነት ካመጣቸው ፣ የማያቋርጥ ተከታታይነት ያለው ፍቅር በቤት ውስጥ እንዲኖር ያስፈልጋል ። ፍቅር ብዙ ጠባዮች አሉት ። በቤት ውስጥ ፍቅር ራሱን በምን አይነት ሁኔታ ይገልጣል ? (ራስ ወዳድና ስግብግብ አለመሆን ፥ ለሌሎቹም ማሰብና



ሌላም በጎነት ማሳየት) ፍቅር ብቻውን ደስተኛ የሆነ ጋብቻን መፍጠር ይችላል ? (ውይይት ይደረግበት ።) ከፍቅር በቀር ሌላም ተጨማሪ ነገር የሚያስፈልግ ይመስላል ። ገላትያ ፭ ፥ ፳፪ እና ፳፫ እናንብብ ። እነዚህ የመንፈስ ፍሬዎች በቤተሰባችን ጠባይ ላይ የሚታዩ ከሆነ በቤታችን ሰላም ደስታ የሚሰፍን ይመስላችኋል ? (ከሆነ — አዎ !)

እለት እለት ኑሮ በጥቃቅን ነገር የሚገነባ ነገር ነው ። ስለዚህ የጋብቻን ደስታ የሚያመጣው የብዙ የጥቃቅን ነገሮች ውጤት ነው ። ባለፈው ትምህርታችን ላይ ጥቂት የጋብቻን ግቦችን ጠቅሰን ተነጋግረናል ። እነዚህ ጥቂት ግቦች ምን ነበሩ ? (ፍቅር ፥ ተባባሪነት ፥ ታማኝነት ፥ ክርስቶስን ማክበር ፥ ዋስትና ፥ መንፈሳዊ ብስለት ወይም እድገት ፥ ሕብረትም አባሪነት ) እነዚህ ነገሮች በእርግጥ ደስታን የሚያበረክቱ ናቸው ። ባልን ወይም ሚስትን ደስ ከሚያሰኙአቸው ጥቃቅን ነገሮች አንዳንዶቹ ምንድር ናቸው ? (በሀሳባቸው ተወያዩበት ።) ከየወላጆቻቸው ቤት ወጥተው አዲስ ቤተሰብ በመፍጠር በአንድነት የሚኖሩ ቤተሰቦች ከወጡበት ቤተሰብ ጋር በሚያደርጉት ሕብረት ደስ ይላቸዋል ። ሁለቱም ቤተሰቦቻቸውን የተው ናቸው ። ሆኖም ሁለቱም አሁንም ቢሆን ቤተሰቦቻቸውን እየወደዱ ስለሆነ ሕብረታቸውን ይፈልጋሉ ። ቤተሰባቸው ዘላቂነት ያለው እንደሆነ የሚያስቡና ሁለቱ ተጋቢዎች እግዚአብሔር እንዳገናኛቸው በመቁጠር ለክርስቶስ ፍቅር ካላቸው ይህ ራሱ ደስታቸውን ያበዛዋል ። ባለቤቱ ምግብ በምታዘጋጅበት ጊዜ ሕፃናቱን በመጠበቅ የእርዳታ እጁን መዘርጋት አለበት ። ሚስትዮዋ ባለቤትዋ የሚወደውን አይነት ምግብ ስታዘጋጅ በዚህ ጥቂት ነገር እንኳ ብዙ ደስታ የሚገኝበት ጊዜ አለ ።

አስደሳች አይነት ጋብቻ ሁልጊዜ የሚፈጸመው ለጋብቻ በተዘጋጁ ሰዎች ነው ። እነርሱም የሥጋና የመንፈስ ብስለት ያላቸው እንደሆነ ነው ። ምሳሌ ፲፰ ፥ ፳፪ና

፲፱ ፥ ፲፬ እናንብብ ። መልካም ወንድ መልካሚትዋን ሴት ሲያገባ ጋብቻው በዚህ ጥቅስ ላይ እንደምናነበው ደስታን በደስታ ላይ ደራርቦ የሚያመጣ ይሆናል ። አንዳቸው ሌላቸውን ከእግዚአብሔር እንደተቀበሉ አድርገው በመቁጠር ከተፈቃቀሩ ውጤቱ ደስታ ይሆናል ።

ሁላችንም ብቻችንን በነበርን ጊዜ እንደጠፉች በግ እንንከራተት ነበርን ። (ኢሳይያስ ፶፫ ፥ ፮) ስለዚህ በትክክለኛው ጐዳና የሚመራን እረኛ ያስፈልገናል ። ደስታ እንዲኖር ከተፈለገ ቤትም የታወቀ መሪ ወይም እረኛ ያስፈልገዋል ። ከባልየው በላይ ክርስቶስ የታወቀ የቤተሰቡ መሪና ራስ መሆን አለበት ። እርሱ ወደ ክፉ ሳይሆን ወደ ደስታ ብቻ ሊመራን ይችላል ። ሁለቱም ተጋቢዎች ጋብቻቸውን የበለጠ ደስተኛ ለማድረግ መጣር አለባቸው ። ደስታ ዝም ብሎ የሚገኝ ነገር አይደለም ። ደስታ ለማግኘት ብዙ ትግል ከማድረግ ይልቅ ደግሞ በጌታ ፊት እያንዳንዳቸው እርሱ እንደሚፈልገው ሆኖ መገኘት የበለጠ ደስታን ያመጣል ። ሁለቱም በሕይወታቸው የመንፈስ ፍሬዎች ያፈራሉ ።

በባልና በሚስት መካከል ያለው ፍቅር ከዓመት ዓመት እየጠነከረና እየጠለቀ ሲሄድ ደስታቸው እየበዛ ይሄዳል ። ከጋብቻ ጋር አብሮ የሚመጣ ችግርና ኃላፊነት አለ ። ቢሆንም ይህ ችግር ደስታቸውን ሊያጠፋ አይችልም ። የተወያዩት ችግር የተከፋፈለ ችግር ነው ። ፈተና ተጋቢዎችን የበለጠ ስለሚያቀራርባቸው አንዳቸው ለሌላቸው ያላቸውን ደስታ ይጨምራል ። ይሄም የሚሆነው ለችግራቸው መፍትሄ ለመፈለግ አብረው ሲጸልዩ ነው ። አንድ ሰው ይኸንን ኃላፊነት ለመቀበል በተማረ ጊዜ ችግሩ ይቃለልለትና ይደሰትበታል ።

<u>ትምህርቱን በሥራ ላይ ማዋል ፦</u>

እግዚአብሔር ጋብቻ ደስ የሚያሰኝ እንዲሆን አቅዶ አል ። የአቶ ኃይሌ ዘመድ የሆኑ ቤተሰቦች ቤት በዚያች ምሽት ለምን ደስተኛ ሳይሆን ቀረ ? (አስተያየታቸውን እንዲሰጡበት ይደረግ ።) አንዳቸው ለሌላቸው ፍቅርን



አያሳዩም ነበር ። ይቅርታ የመደራረግ መንፈስ አልነበራቸውም ። በሁለቱም መንፈሳዊ ብስለት አይታይባቸውም ። አወጣጥዋ ለመልካም ነገር ቢሆን እንኳ ሚስትየዋ የቤተሰብዋን ኃላፊነት ቸል ትለዋለች ። ባልየው ደግሞ ለምን ወደ ውጭ እንደወጣች ሳያረጋግጥ ይበሳጫል ፣ ይቆጣልም ። ሁለቱም ራሳቸውን ብቻ የሚወዱ ስለሆኑ አንዳቸው ለሌላቸው ወይም ስለ ልጆቻቸው አያስቡም ። ማንኛውም ጥቃቅን ግጭት የዚያን ቤት ሕብረት በማቃወስ ሰላም ያሳጣቸው ነበር ። ነገር ግን ታላቁን ደስታ የሚያመጣውን ታናሹን ነገር ከማድረግ መቆጠብ የለባቸውም ።

<u>ጸሎት</u> ፦ እግዚአብሔር በየጥቃቅኑ ነገር እንድንተሳሰብና ጉዳዩን ሳናረጋግጥ ለቁጣ እንዳንቻኮል ወይም ፈጥነን ፍርድ እንዳንሰጥ ማስተዋልን በመስጠት እንዲረዳን እንጸልይ ።

## ክፍል ፬ — ትምህርት ፲፪

# ሠርግ

<u>የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል</u> ፦ ዮሐንስ ፪ ፥ ፩ — ፲፩

<u>የቃል ጥናት</u> ፦ ዮሐንስ ፪ ፥ ፪

<u>ዓላማ</u> —.ክርስቲያኖች ሠርጋቸው ክርስቶስን የሚያስከብርና ላላመኑት ሰዎች ጥሩ ምስክርነት ያለው እንዲሆን ለማድረግ

<u>መግቢያ</u> ፦ ጊዜው እንዴት ተፋጠነ እባካችሁ ! ለሠርጉ ዝግጅት የሚደረጉ ብዙ ነገሮች አሉ ። በኤልሳቤጥ ረዳትነት ጽጌ የሚያምር ነጭ ከፈፍ ያለውንና ወተት የመሰለውን ቀሚስ ከነነጠላው እየሰፉች ነው ። እርስዋም ይሄን አይነት ልብስ የመረጠችው ለብዙ ዓመት የአዘቦት ልብስ አድርጋ እንደምትጠቀምበት ስለምታውቅ ነው ። አንዳንድ ልጃገረዶች ነጭና ውድ ዘርፋፋ ቀሚስ ከነመጎናጸፊያው መግዛትን ሲመርጡ የቀሩት ደግሞ እንደችሎታቸው የሠርግ ልብስ

ያዘጋጃሉ ። እርስዋም በሠርግዋ ጊዜ ዋናው ተፈላጊ ነገር ልብሱ እንዳልሆነ ታውቃለች ።

ጥላሁንና ጽጌ በአንድነት ሆነው የዘመዶቻቸውንና የጓደኞቻቸውን ስም በጥሬው ወረቀት ላይ እየጻፉ አሳደልዋቸው ። በእርግጥ በሠርጋቸው በአል ላይ ሊገኙ የሚፈልጉዋቸው ብዙ ወዳጆች አልዋቸው ። ሆኖም ሁሉንም ቢጠርዋቸው ብዙ ገንዘብ ስለሚያባክኑና ኋላ ለብዙ ወራት ሊከፍሉት በማይችሉ እዳ ውስጥ ስለሚገቡ እግዚአብሔር አይከበርበትም ።

እነርሱም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚከናወን የጋብቻ ሥነ ሥርአት እንዲፈጸምላቸውና በመንደራቸው ሽማግሌዎች ፊት ፊርማቸውን እንዲፈራረሙ ይፈልጋሉ ። አንዳንዶቹ ለሠርጉ በአል የተጠሩት ሰዎች አማኞች አልነበሩም ። ስለዚህም የሠርጋቸው በአል መልካም ምስክርነት እንዲሆንላቸው ይፈልጋሉ ። ጋብቻ የተቀደሰ ስለሆነ የእነርሱም የጋብቻ በአል የተቀደሰ እንዲሆንላቸው ይፈልጋሉ ። እነርሱም በቤተ ክርስቲያን የመጋባቱ ጉዳይ የቅድስናው ተካፋይ እንደሚያደርጋቸው ይሰማቸዋል ። በጋብቻቸው በአል ላይ ለክርስቶስ ክብር የማይሆን አንዳችም ሥርአትና ወግ እንዲደረግ ጨርሶ አይፈልጉም ።

የጥላሁን ወላጆችና እህቶቹ ከሠርጋቸው በፊት ሁለት ቀን አስቀድመው መጥተው ነበር ። እነርሱም ጽጌንና ቤተሰቦቿን በመገናኘታቸው በጣም ደስ አላቸው ።

አሁን የሠርጉ ቀን ደረሰ !

ትምህርት ፡— እንግዶቹ በጸጥታ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከተሰበሰቡ በኋላ ተነስተው ሁለት የምስጋና መዝሙሮችን ለጌታ ዘመሩ ። ከዚያም በመቀጠል የምስጋና ጸሎት ከተደረገ በኋላ እንግዶቹ ሁሉ እንደቆሙ ጥላሁንና ጽጌ ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ገቡ ። እነርሱም በኤልሳቤጥ ፣ በማሚቱና በጥላሁን ጓደኞች በገብሬና በጴጥሮስ ታጅበው ነበር ። ሁለቱ የጽጌ ታና



ናሽ እህቶች በቅርጫት አበባ ተሸክመው ነበር ። ልጃገረዶቹ በሞላ ሰማያዊ ክፈፍ ያለው ነጭ ቀሚስ ለብሰዋል ። ጥላሁንና አጃቢዎቹ ግን ጥቁር ሱፍ ለብሰዋል ። የሠርገኛዎቹ አጃቢዎች በቤተ ክርስቲያኑ ፊት ለፊት እንደተሰበሰቡ ከእንግዳዎቹ ጋር በሕብረት ዘመሩ ። ዜማውም ፡— «ክርስቶስ ራስና አውራ የሆነበት ቤት ደስተኛ ነው» የሚል ነበር ። መጋቢ ደስታም እንግዶቹ እንዲቀመጡ ከነገርዋቸው በኋላ የሠርጉ አጃቢዎች ደግሞ በግማሽ ዙርያ በመሆን ፊታቸውን ወደ መድረኩ መልሰው በየወንበሮቻቸው ላይ ተቀመጡ ።

«በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ ሁለት ላይ ስለ አንድ ክርስቲያን ጋብቻ በአል እናነባለን ። በዚያን ቀን በተጋቡት ሙሽሮች በአል ላይ ልዩ የሆነ ክቡር ሰው በግብዣው ላይ ተገኝቶ ነበር ። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በዚያ ነበር ። እርሱም በዚያ ግብዣ ላይ እንዲገኝ የተፈለገና የተጋበዘ ነበረ ። በዚህ ዛሬ ደግሞ በሁለት ወጣቶች ጋብቻ ላይ ተገኝተን የጋብቻቸው ምስክሮች ስንሆን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የተጋበዘ እንግዳ ሆኖ በመካከላችን ተገኝቶአል ።»

እጃቸውን ወደ ጥላሁንና ወደ ጽጌ በመዘርጋት ፡— «ዛሬ ወደ አዲሱ ቤታቸው ክርስቶስን ይዘው ቢገቡ ከማንኛውም ነገር የላቀ አስፈላጊ ጉዳይ ነው» ሲሉ ተናገሩ ። እንደገና ደግሞ ወደ እንግዶቹ ዞር ብለው ምናልባት ከመካከላቸው ክርስቶስን እንደ ግል አዳኙ አድርጎ ያልተቀበለ ቢኖር ወደ ሕይወታቸው እንዲቀበሉት ይህ ጥሩ አጋጣሚ ጊዜ ነው ብለዋል ።

በዚህ በቃና በተፈጸመው ሠርግ ላይ ጌታችን ኢየሱስ እጥረት በገጠማቸው ጊዜ ረድቶአቸዋል ። ለእንግዶቹ የሚሰጥ የወይን ጠጅ ባለቀባቸው ጊዜ ክርስቶስ በተአምር ውኃውን ወደ ወይን ጠጅ ለውጦ ጋብዘአቸዋል ። ይህ ተአምር ሊፈጸም ችሎአል ። ምክንያቱም አገልጋዮቹ በቅደም ተከተል ታዘውት ስለነበረ ነው ። በውጤቱም በረከት ሆነላቸው ። ይህም ተአምር ክርስቶስ

ለመጀመሪያ ጊዜ ቤተሰብ ሲመሠረት ያደረገው ተአምራቱ ነው ። ክርስቶስ በዚህ ሥፍራ መገኘቱ ቤተሰብን የመመሥረቱ ጉዳይ ጠቃሚ እንደሆነ አያስረዳንም ?

«ከዚያም ጥላሁንና ጽጌ በቤታቸው ጌታን ባስከበሩት መጠን እየባረካቸው ይሄዳል ። ይሄም ማለት ከችግርና ከፈተና ነፃ ይሆናሉ ማለት አይደለም ፣ ነገር ግን እርሱ ከሚገጥማቸው ማናቸውም ችግር ሊያድናቸው ዝግጁ ነው ።»

ከዚያም ለተጋቢዎቹ አጠር ያለ ጥብቅ ማሳሰቢያ ከተሰጣቸው በኋላ ሙሽሮቹ የቃል ኪዳን መኃላ ለማድረግ ተነስተው ቆሙ ። ይህን በማድረግ ጥላሁን የቤተሰቡ ራስ እንደመሆኑና ጽጌ ደግሞ ታዛዥ እንደመሆንዋ ሁለቱም በአንድነት የክርስቶስ ታዛዦች ናቸው ። እንዳቸውም ሌላቸውን ሞት እስኪለያቸው ለማፍቀርና ለመንከባከብ ቃል ኪዳን አደረጉ ።

መጋቢ ደስታ የእግዚአብሔር በረከት በእነርሱ ላይ እንዲሰፍንና ሊሰጣቸው ያለውን ቤተሰብና ቤታቸውን እንዲባርክ በሚጸልዩላቸው ጊዜ ሁለቱም ተንበርክከው ነበር ። እርሳቸውም በጸሎታቸው እንደቀጠሉ ዝግ ባለ ሁናቴ «እንደበጎች እረኛ ምራን» የሚለው መዝሙር ይዘመር ጀመር ።

እነርሱም ከተንበረከኩበት ተነስተው ፊታቸውን ወደ እንግዶቹ ሲያዞሩ ፊታቸው በደስታና በፈገግታ ያንጸባርቅ ነበር ። ሙሽሮቹ ከቤተ ክርስቲያኑ ወጥተው ወደ ውጭ ሲያመሩ እንግዶቹ ሁሉ በያሉበት ቆመው ነበር ። ሙሽሮቹም ወጥተው በውጭ እንደቆሙ ይህን የደስታ ቀን ከእነርሱ ጋር ለመካፈል የመጡት እንግዳዎች መልካም ቤት ይሆንላቸው ዘንድ እየተመኙ ሰላምታ ይሰጡአቸው ነበር ።

## ትምህርቱን በሥራ ላይ ማዋል ፦

ከዚያም የቤተ ክርስቲያኑ ወይዛዝርት ኮካ ኮላና ዳቦ ለእንግዶቹ ያድሉ ጀመር ። ያም ግሩም ጊዜ ስለነበረ



እያንዳንዱ ሰው የክርስቶስ በዚያ ሥፍራ መገኘት ይሰማው ነበር ። እንግዳዎቹ ከተበተኑ በኋላ የሙሽራዎቹ አጃቢዎችና ቤተሰቦች እንዲሁም የቅርብ ጓደኞቻቸው እነጥላሁን ሊኖሩበት ወዳለው ቤት ሄደው የእራት ግብዣ ተደረገላቸው ። ያም ጊዜ በጣም ከሚቀርቧቸውና ከሚወድዋቸ ጋር ማንኛውንም ነገር የሚከፋፈሉበት ጊዜ ነው ። እነርሱም በጋብቻቸው ሥነ ሥርአትና በእራት ግብዣቸው ላይ ጌታን ሊያስከብሩት ይፈልጋሉ ። እነርሱም ጌታ በቤታቸው እንደሚከበርና ቤታቸውን እንደሚባርክ ያውቃሉ ።

ጸሎት ፦ ወጣቶች ጋብቻችሁ ጌታን የሚያስከብርና ጥሩ ምስክርነት እንዲኖረው ጸልዩ ።

ወላጆች የልጆቻችሁ ጋብቻ ከሥረ መሠረቱ ጀምሮ በእግዚአብሔር የተወጠነ እንዲሆን ጠይቁት ።



መበለትዋ ወ/ሮ በላይነሽ ከልጆችዋ ጋር



## ክፍል ፫
## ትምህርት ፲፫
## እንደገና መጋባት

<u>የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል</u> ፦ ሩት ፫ ፣ ፲ ፤ ፩ኛ ጢሞቴዎስ ፭ ፣ ፫ — ፮ ፤ ም. ፭ ፣ ፱ — ፲፮

<u>የቃል ጥናት</u> ፦ መዝሙር ፻፵፮ (፻፵፭) ፣ ፲፱

<u>ዓላማ</u> —. እግዚአብሔር መበለቶች ዳግመኛ እንዲያገቡ እንዳበረከተላቸው ፣
.ጋብቻቸውንም ያለ ሞትበስተቀር ምንም ነገር እንደማያቋርጠው ለማስረዳት

<u>መግቢያ</u> ፦ በአንዳንድ ጉዳዮች ላይ ለመወያየት ወይዘሮ በላይነሽ ወደ መጋቢ ደስታ ዘንድ ሄዱ ። እርሳቸውም በአንዳንዶቹ የጋብቻ ትምህርት ክፍለ ጊዜ ገብተው ተምረው ስለነበር አሁን ደግሞ ተጨማሪ ምክር ስለሚያስፈልጋቸው መጥተዋል ። ከሁለት ዓመት በፊት ባለቤታቸው በሥራ ላይ እንዳሉ በደረሰባቸው አደጋ ሁለት ልጆች ጥለውባቸው ሞተዋል ። ቤተሰብን ማስተዳደር ሁልጊዜ ስለማይቀል በችግር ምክንያት አንዳንድ የእጅ ሥራቸውን ሸጠዋል ። አንዳንዴም ዘመድ አዝማድ የልግሥና እርዳታውን ያደርግላቸዋል ። አንዳንድ ጊዜም ከቤተ ክርስቲያን ጥቂት ገንዘብ ያገኛሉ ። ቢሆንም በዚህን ጊዜ በጣም ያወከቸው ነገር የገንዘብ ጉዳይ አልነበረም ። ሚስታቸው በሞት የተለዩአቸው አቶ ሺፈራው ለጋብቻ ይፈልጓቸዋል ። እርሳቸውም ይህ ነገር ለእርሳቸውና ለአቶ ሺፈራው እንዲሁም ለልጆቻቸው መልካም እንደሆነ ለማረጋገጥ ይፈልጋሉ ።

<u>ትምህርት</u> ፦ መጋቢ ደስታ ስለ መበለቶች የሚያስተምሩ ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ለወይዘሮ በላይነሽ አሳዩዋቸው ። በመበለትነት የኖረችውን የሩትን ታሪክ ከብሉይ ኪዳን ጠቅሰው አስረዱዋቸው ። ከትውልድ ሀገርዋ እጅግ ብዙ ሩቅ ከሆነ ሥፍራ እግዚአብሔር ባል አዘጋጀላት ። በተከታታይ የሆኑት ነገሮች ሁሉ በእግዚአብሔር እቅድ ውስጥ የተደረጉ ናቸው ። ከቦአዝ

ጋር እንድትጋባ በእግዚአብሔር ተመራች ። እግዚአብ ሔርም የዳዊት አያት የሆነውን ኢዮቤድን ሰጣቸው ። ክርስቶስም ከዳዊት ዘር ተወለደ ።

(፩ኛ ጢሞቴዎስ ፭ ፥ ፲፬ — ፲፮ ይነበብ ።) ሚስቶቻ ቸው የሞቱባቸው ወንዶችና መበለቶች ሁሉ ዳግመኛ ያገቡ ዘንድ የእግዚአብሔር ፈቃድ አይደለም ። ነገር ግን ለአንዳንዶቹ የእርሱ እቅድ ነው ። ጳውሎስ ልጅነት ያላቸው መበለቶች እንዲያገቡ ያበረታታቸዋል ። ምክን ያቱም ሥጋቸው ገና አፍላ ስለሆነ እግዚአብሔር ገና በልጅነት ብቻዬን አስቀረኝ ብለው ስለሚያማርሩት ነው ። ከዚህም በቀር ሰነፎችና ዘዋሪዎች እንዳይሆኑ ጳውሎስ እንደዚህ ያሉት ሴቶች ቢያገቡና ለባሎቻቸውና ለልጆቻ ቸው አገልግሎት ቢሰጡ መልካም ነው ። ይኸውም ስለ ራሳቸው በማሰብ እንዳይጨነቁና ሀሳባቸውን ሌላ ሰው እንዲያስቡበት ለመቀየር ነው ። መበለቶችን የሚረዳ ዘመድ ከሌላቸው እነርሱን ለመርዳት ቤተ ክርስቲያን ኃላፊነት አለባት ። (ቁጥር ፲፮) በድኅነት ደረጃ ያሉ ትንም ቤተ ክርስቲያን የመርዳት ኃላፊነት አለባት ። እንደ አጋጣሚ ሆኖ ዘመድ የሆኑ ሰዎች ሁሉ የመበለት ዘመዳቸውን ኃላፊነት አይቀበሉም ። ሁሉን ነገር ለመ ሥራት ቤተ ክርስቲያኑን ይፈልጉታል ።

ወይዘሮ በላይነሽ ለአቶ ሺፈራው ታላቅ አክብሮት አላቸው ። ነገር ግን አቶ ሺፈራውን ለማግባት የሚገባ ውን ያህል ፍቅር ይኖራቸው እንደሆን አያውቁም ። እርግጥ ቢያገቡአቸው ለራሳቸውና ለልጆቻቸው አንዱ ሚቀልላቸው ያውቃሉ ። ነገር ግን ይሄ የጋብቻ መሠረቱ እንዳልሆነ ያውቃሉ ። የቀድሞ ባለቤታቸውን ከልባ ቸው ይወድዋቸው እንደነበረ እርግጠኛ ናቸው ። ዳግ መኛ ቢያገቡ የቀድሞ ባላቸውን እንዳዋረዱ ይቆጠርባ ቸው ይሆን ?

መጋቢ ደስታ ከ፩ኛ ቆሮንቶስ ፯ ፥ ፴፱ ላይ አነበቡ ፡— «ባለቤትዋ በሕይወት እስካለ ሚስት የባልዋ እኳል ናት ። ባለቤትዋ ከሞተ ግን ሌላ የማግባት መብት አላት ፥ ያውም የሚፈቀደው ክርስቲያን ያገባች እንደሆነ ነው ።»



«እርሶም ሆነ አቶ ሺፈራው ክርስቲያኖች ናችሁ ። ቢሆንም እርሶዎ የራሶን ችግር የሚወጡበትን ዘዴ አሰቡ እንጂ የአቶ ሺፈራውን ችግር ለማቃለል አላሰቡም ። ልጆችን በማሳደግ በኩል የሚረዳዎት ሰው ያስፈልጎ ታል ፥ በተመሳሳይ ጊዜ ደግሞ እርሶዎ ለአቶ ሺፈራው ያስፈልጓቸዋል ። ትዳራቸውን የምታቋቁምላቸው ሚስት ታስፈልጋቸዋለች ። እርሶዎም ደግሞ ችግሮዎን ለመወ ጣት ብቻ ከእርሳቸው ጋር ከኖሩ ፤ በአንዳንድ ሁኔታ እር ስዎ እንዳሰቡት ካልሆነ ፤ የቀድሞ ባልዎን በማስታወስ ፤ ከሌላ ባል ጋር ብኖር የበለጠ ይመቸኝ ይሆን ? ብለው ማሰብዎ አይቀርም ።»

የጋብቻ አንድነት የሚያቋርጠው ሞት ብቻ እንደሆነ ለወይዘሮ በላይነሽ አብራሩላቸው ። ምንም እንኳን የቀ ድሞ ባላቸውን በጣም አድርገው ቢወዱአቸውም ሌላው ንም መውደድ መማር ሊኖርባቸው ነው ። ምናልባት ዳግመኛ ያገቡ ከሆነም የቀድሞ ባላቸውን ማቃለል የለባ ቸውም ።

እግዚአብሔር ልጆቹ ሁሉ ደስ እንዲላቸው ይመ ኛል ። የማይገባ አይነት ችግር እንዲደርስባቸው አይፈ ልግም ። መጋቢ ደስታ እግዚአብሔር ለወይዘሮ በላይነ ሽና ለልጆቻቸው እንዲሁም ለአቶ ሺፈራው ተገቢውን ዝግጅት እንደሚያደርግላቸው ያምናሉ ። እርሳቸውም ወይዘሮ በላይነሽን ጌታ አቶ ሺፈራውን እንዲያገቡ ፈቃዱ ከሆነ ጥርጣሬን ሁሉ ከአእምሮአቸው አስወግዶ ለአቶ ሺፈራው የጠለቀ ፍቅር እንዲኖራቸው ማድረግ እንደሚችል ነገሩዋቸው ።

መፋታትን የሚያስከትል ዳግመኛ ጋብቻ ውስጣዊ ችግር ያለበት እንደሆነ መጋቢ ደስታ ጠቁመዋል ። የእግዚአብሔር ትእዛዝ ግን እግዚአብሔር አንድ ያደረገ ውን ሰው እንዳይለየው ነው ። (ማርቆስ ፲ ፥ ፱) የጋብ ቻው ሕብረት እንዳይፈርስ ይከለክላል ። ሆኖም በዚህ ጉዳይ ላይ ለእግዚአብሔር የማይታዘዙ ብዙ ናቸው ።

መፋታት ደስተኝነት የሌለውን የጋብቻ ችግር በሞላ ሊያቃልል አይችልም። አንዳንድ ሰዎች ከተፋቱ በኋላ ኑሮ የበለጠ ለሕይወታቸው መራራ ሆኖ አግኝተውታል። አሁንም ፊቶ እንደገና ማግባት ደግሞ የበለጠ ለእግዚአብሔር አለመታዘዝ ነው። ማንኛውም ለእግዚ. አብሔር የማይታዘዝ ሰው በሕይወቱ ላይ የእግዚአብሔር በረከት እንደሚመጣ አድርጎ አይጠብቅ። ነገር ግን ሁለቱ ጌታን የሚወዱ ሰዎች በእግዚአብሔር ፈቃድ በጋብቻ ሲጣመሩ የእግዚአብሔር በረከት በእነርሱ ላይ ይሆናል።

<u>ትምህርቱን በሥራ ላይ ማዋል</u>፥—

ወይዘሮ በላይነሽ መጋቢ ደስታ ከእግዚአብሔር ቃል ጠቅሰው ስለመከሩዋቸው ከልብ አመስግነዋቸዋል። እርሳቸውም እግዚአብሔር ለእቶ ሺፈራው ፍቅር እንደ ሰጣቸው ያውቃሉ። ከዚህም በቀር እርሱ ለእርሳቸው እና ለልጆቻቸው የቆሳቁስና የሥጋ ጥቅም የሚሰጡ ነገሮችን እንዳዘጋጁ ያውቃሉ።

<u>ጸሎት</u>፥— እግዚአብሔር ለመበለቶችና ሚስቶቻቸው ለሞቱባቸው በሕብረተሰብም ሆነ በቤተ ክር ስቲያናችሁ እንድታስቡና እንድትቆረቆሩ እንዲያደርጋ ችሁ ጠይቁት።